# ርኆቦት

በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በሚኒሶታ የሚዘጋጅ ቁጥር 18 April/2008



## ከአቶ ስዩም ቤተሰብ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ



ከደም ካንሰር ተፈወስኩ



ከጠላት እስራት ነጻ ወጣሁ

★ ድብቅ እንባዎች

★ ወርቃማ ቃል

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| ከአዘጋጅ | 1 |
| እግዚአብሔርን ማገልገል | 3 |
| እየሱስ ለእኔም መልካም ነው | 4 |
| ጻድቅ በጭንቅ የሚድን ከሆነ | 5 |
| ከወንድም ስዩምና ከእህት ዘውዲቱ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ | 8 |
| ከጠላት እስራት ነጻ ወጣሁ | 10 |
| ዜና ርሆቦት | 12 |
| ድብቅ እንባዎች | 14 |
| የሰው የተፈጥሮ ባህርይ | 16 |


## ለህይወት አንድ መንገድ ብቻ

ዮሃ 14፤6... ኢየሱስም እኔ መንገድና እውነት ህይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም...
ይህ መንገድ ከሌሎቹ መንገዶች በምን ይለያል?

1. ይህ መንገድ መውጫ አለው ብዙ ሰው ከመጠጥ ከድራግ ከሃጢያት የሚወጣበትን መንገድ ይፈልጋል ኢየሱስ ከዚህ ችግር ሰዎችን የሚታደግ ጌታ ነው በጠላት ከሚኮነኑ ከሚከሰሱ ተስፋ ከሚቆርጡ በባዶነት ከሚጠቁ በመጨረሻም ከመንፈሳዊ ሞት  የመውጫ መንገድ ኢየሱስ ነው

2. ይህ መንገድ መግቢያ አለው  ዮሃ 14፤6 ላይ... በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ይላል በመንግስተ ሰማይ ለዘላለም ለመኖር በዚህ ምድር ሆነን የምንወስን ከሆነ  የምንገባበት መንገድ ኢየሱስ ነው ኢየሱስ ወደ ህይወት እና ወደ ፍቅር መግቢያ መንገድ ነው ያለ ኢየሱስ ህይወትና ፍቅር የሚባል ነገር የለም ኢየሱስ ወደ ተስፋና ወደ ሰላም መግቢያ መንገድ ነው ያለ ኢየሱስ ተስፋና ሰላም የለም በዚህ መንገድ ታሪክ ሲያልቅ ሰው ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ይሆናል

ስለዚህ በዚህ ዓለም ካለው እስራት መውጫ መንገድ ኢየሱስ ነው ሰይጣን ያሰረውን ሃጢያት ያሰረውን ዓለም ያሰረውን ዕውቀት ሊፈታው አይችልም አንድ የማምለጫ መንገድ ብቻ እርሱም ሞትን ድል አድርጎ በአብ ቀኝ የተቀመጠ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ጊዜ አይውሰዱ ዛሬ ስሙን ጠርተው አድነኝ ቢሉና ልቦዎን ከፍተው ቢቀበሉት
በደሙ አጥቦ ልጁ ያደርገዎታል!!

# ✍ ከአዘጋጅ

ቃሉን ስበክ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና ፈጽመህ እየታገስህና እያስተማርህ ዝለፍና ገስጽ ምክርም ህይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሱበት ዘመን ይመጣልና ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ እንደገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ መከራን ተቀበል የወንጌል ሰባኪነትን ስራ አድርግ አገልግሎትህን ፈጽም"
2ኛ ጢሞቲዎስ 4፤ 2-5 "

ካስተዋልኩት አስር (10) ነጥቦች

1. መዝሙር መውደድና መዘመር ህይወታችን እንዳያድግና እንዳያፈራ ምክንያት አይደለም

በዝማሬ እግዚአብሔርን እናመልካለን እናመሰግናለንም፤ ጌታ ኢየሱስ ወደ መስቀል ከመሄዱ በፊት ከደቀመዛሙርቱ ጋር ዘመረ ማርቆስ 14፤26 ዝማሬ የእግዚአብሔርን ክብር ያወርዳል፤ ዝማሬ ድብቅን ጦር ያስመጣል (መ.ዜ.መ.ካ. 20፤22 "ዝማሬውንና ምስጋናውን በጀመሩ ጊዜ ይሁዳን ሊወጉ በመጡት በአሞንና በሞአብ ልጆች በሴይርም ተራራ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ድብቅ ጦርን አመጣባቸው)፤ ዝማሬ የተዘጉ ደጆችን ያስከፍታል (ሓ.ሰ. 16፤25/26 "በመንፈቀ ሌሊት ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር... ድንገትም የወህኒው መሰረት እስኪናወጥ ድረስ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ በዚያን ጊዜ ደጆች ሁሉ ተከፈቱ")፤ ዝማሬ መልእክትን ከሰማይ ያስመጣል፤ ዝማሬ ክፉን መንፈስን ያባርራል፡፡ መጽሓፍ ቅዱሳችን ዝማሬ ክፉን መንፈስ እንዲሚያባርር ነው እንጂ ዝማሬን ክፉ መንፈስ እንደማይፈራው አልጻፈልንም እርግጥ ነው ህይወታችንና ንሮአችን የተበላሸ ከሆነ እንኳን ዝማሬያችን ስበከታችንም ሆነ ጸሎታችን ጠላትን አያስፈራውም በመጽሓፍ ቅዱሳችን ላይ ስንመለከት ጳውሎስ በሚሰብከው በእየሱስ እናምላችኋለን እያሉ ክፉ መናፍስት ባሉባቸው ላይ የጌታ የእየሱስ ክርስቶስ ስም ሊጠሩ በሞከሩ ጊዜ ክፉ መንፈስ ግን መልሶ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ እየሱስንም አውቀዋለሁ እናንተ እነማን ናችሁ ነው? ያለው ሓዋ ስራ 19፤13-17፡፡ እዚህ ላይ የሚገርመው ሲዘምሩ ሳይሆን ሲጸልዩ ነው፡፡ ችግሩ የህይወት ጉዳይ እንጂ የመዝሙሩ ጉዳይ አይደለም ስለዚህ እውነተኛውን የክርስቲያንን ንሮ ማስተማር እንጂ ዝማሬን አላስፈላጊ ማድረግ በመጽሓፍ ቅዱስ የተጻፈውን መቀነስ ይመስለኛል፡፡ መዝሙር ለምትወዱም ለምን እንደምትወዱ ራሳችሁን እንድትጠይቁ እወዳለሁ ለሙዚቃ ፍቅር ነው?፤ ለታይታ ወይም ለዝና ነው? በዓለም ጥላችሁት የመጣችሁትን የተካላችሁ ስለመሰላችሁ ነው?፤ ለመሆኑ የምትዘምሩለትን ታውቁታላችሁ? ትኖሩለታላችሁ?፤ በእውነት የምትዘምሩት በህይወታችሁ እውነት ሆኖ አግኝታችሁታል? ካልሆነ ከወዴት እንዳለችሁ ራሳችሁን አውቃችሁ በእውነትና በመንፈስ ትዘምሩ ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳችሁ፡፡

2. ከተሳሳተ ጋብቻ ለመጠበቅ ወይም በህይወታችን እግዚአብሔርን የመጀመሪያ ለማድረግ ጋብቻን ከማጣጣል መቆጠብ ይኖርብናል

ጋብቻን የመሰረተ እግዚአብሔር እንጂ የተዋደዱ ሰዎች የመሰረቱት አይደለም ("እግዚአብሔር አምላክም አለ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት" ዘፍጥረት 2፤18) መጽሐፍ ቅዱሳችን ጋብቻ ክቡር ነው መኝታውም ንጹህ ነው ይላል፡፡ ታዲያ ይህ እግዚአብሔር ያከበረውን ዛሬ ዘመናችን ክቡርነቱን እንዴት እየገለጸው ነው? ግን እኛ ልናደርግ የሚገባን እግዚአብሔር የሰራውንና ያከበረውን ልናከብርና ልንጠነቀቅለት እንዲሁም ዋጋን ልንከፍልለት ይገባል፡፡ እግዚአብሔር በትዳር የባረካችሁ ልታመሰግኑና እግዚአብሔር የሰራው መልካም መሆኑን እንድታሳዩ ልታደርጉ የሚገባችሁ ትዳር ስራ ነውና ከእግዚአብሔር ጸጋ ጋር ትዳራችሁን እየሰራችሁ ምስሌ ልትሆኑ ይገባል፡፡ ያላገባችሁም እግዚአብሔር በጌዜው ሁሉን ውብ አድርጎ ስለሚሰራ በጊዜው ያማረውን ሊሰጣችሁ ነው እንጂ የዘገያችሁት ጋብቻ ትርፍ ነገር ስለሆነና ስለማያስፈልግም እንዳይደለ በመገንዘብ ጌታ በሰራው እያመሰገናችሁና እያከበራችሁ አፋችሁንም ከስንፍና ንግግር በመቆጠብ ጌታን ጠብቁ እላለሁ፡፡

3. ወንጌላችን የብልጽግና ወንጌል ብቻ አይደለም ለማለት ሃብትንና በተሻለ ንሮ መኖርን መቃወም አይኖርብንም፡፡

በረከት ከእግዚአብሔር ነው፡፡ የሰው የእጁን ስራ፤ አእምሮን የሚባርክ እግዚአብሔር ነው ግን በትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ሃብትን ማግኘት መባረክ አይደለም መጨረሻውም የከፋ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ነፍሳችን ከስታ ገንዘብን ብናከማች እሱም ሌላ ጉዳት ነው እንጂ በረከት አይሆንም በተረፈ እግዚአብሔር ቢባርክ እግዚአብሔር ባደረገው ሊከበር እንጂ የሰጠውን ስጦታ መቃወም ተቃውሞው ሃብትን ሳይሆን ሰጪውን ይመስላል ሌላው ደግሞ ሃብት የሌለውን እግዚአብሔር አልባረክህም ልንል አንችልም የእግዚአብሔር በረከት ብዙ ናትና በረከትን ከሃብት ጋር ብቻ ማዛመድ መሳት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

4. እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ምህረት፤ ነው የሚባላም እሳትም ነው፡፡

ግን ንስሃ ለሚያስፈልገውና አቅጣጫውን መቀየር ለሚያስፈልገው እግዚአብሔር ፍቅር ነው ማለት፤ ፈውስና መጽናናት ለሚያስፈልገው እግዚአብሔር የሚባላ እሳት ነው ብለን ብንነግረው በወንጌል ሃይል ሰዎች ካላቸው እስራት እንዳይፈቱ መሰናክል እንሆናለን፡፡ ጌታ እየሱስ ክርስቶስ በምድር ሲመላለስ ሃጢያተኛውን ደግመህ ሃጢያት አትስራ እያለ ሲያሰናብት፤ በስጋ ምግብ የሚያስፈልጋቸውን ሲመግብ፤ አጋንንት ያደሩባቸውን ነጻ ሲያወጣ፤ መጽሓፍን አጥርቼ አውቃለሁ ብሎ በቤተመቅደሱ ለማይጠፋውም ደግመህ በውሃና በመንፈስ ካልተወለድህ በቀር ወደ እግዚአብር መንግስት መግባት አትችልም እያለ፤ የገንዘብ ፍቅር ያለበትንም ሁሉን ሽጠህ ተከተለኝ እያለ፤ ፈሪሳውያንንም የተለሰነ መቃብር ናችሁ ብሎ የወደቁበትን እያሳየ፤ ማርያም ውድ ሽቱ ሰብራ በእግሩ ላይ ባፈሰሰች ጊዜ ለድሆች ተቆርቋሪ መሳይ ተነስቶ ለምን ተሸጦ ገንዘቡ ለድሆች አይሰጥም ሲል መልካም አደረገች እያለ፤ ሌሊቱን እየጸለየ አገልግሎቱን ፈጸመ ዛሬም ለኛ ይህ ይሁንልን፡፡

5. ሙሉ ወንጌልን መስበክ

የሳተን ይመልሳል፤ ሃጢያተኛን ወደ ንስሃ ይመራል፤ መጽናናት ለሚያስፈልገው መጽናናትን ይሰጣል፤ ሰዎችን ወደ ዘላለማዊ ህይወት ይጠራል፡፡ ስለዚህ የራሳችን ወይም የግል አመለካከታችንን መስጠት ጠቃሚና ትምህርት ሰጪ የሆኑበት ቦታዎች ቢኖሩትም ያለቦታው ከሆነ ደግሞ ከማነጽ ይልቅ ለማፍረስ ጉልበት አለው ብዬ አምናለሁ ፤ በሰዎች ልምምድ ውስጥ ራስን ማስገባት ደግሞ ሌላው አደጋ ነው፡፡ ምክንያቱም የሌሎቹ ልምምድ በምን እንዳለፉና በምን ዓይነት ኑሮ እንደኖሩ ስለማናውቅ እነሱ ለሆነባቸውና ለሆነላቸው ነገር ሌላው ይሆንበታል ወይም ይሆንለታል ማለት አደጋ ነው፡፡

በራሳችን ወይም በመሰለን ነገር ለእግዚአብሔር ስራ በመቅናት የምናገለግል ከሆነ የምናገለግላቸውን ሰዎች ወደ እልከኝነትና ትክክል ወደ አልሆነ አቅጣጫ ይመራቸዋል ብዬ አስባለሁ ምክንያቱም ዳዊትን ስንመለከት በዘመኑ የእግዚአብሔርን ሃሳብ አገልግሎ ነው ያለፈው ዛሬም በዘመናችን የእግዚአብሔር ቅንዓት ወይም መሻት ሃሳቡን የሚያገለግልን ነው እንጂ የኛን ቅንዓት ወይም የልብን መሻት አይደለም መልካምና ትክክል ለኛ የመሰለን ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው ማለት አይደለም ስለዚህ ዛሬ በዘመናችን የሚያስፈልገው በጊዜውም ያለጊዜውም ቅልቅል የሌለበትን ማለት ከኛ አመለካከት ጋር ያልተዛመደውን ንጹህና ሙሉ የሆነውን ወንጌል መስበክ ሰባኪውንም ህዝቡንም ነጻ ያወጣል ብዬ አስበላሁ፡፡

6. እኛ እንዲሆን የፈለግነው ስላልሆነና የእኛ እጅ ካልተባበረች

በሚሆነውና በሚደረገው ነገር ውስጥ ሁሉ እግዚአብሔር የሌለ ከመሰለን ራሳችንን ያስቀመጥንበት ስፍራ ትክክለኛ ስላልሆነ ቆም ብሎ ማሰብ ይጠቅማል። ክብር ለእግዚአብሔር እንዲመጣ ከፈለግን የውስጣችንም ጩኸት እግዚአብሔር ከብሮ ማየት ከሆነ ስራው በምንም ሆነ በማንም ይሰራ በተሰራው ስራ ነፍሳችን ሓሴት ማድረግ ይገባታል።

7. ኑሮአችን መጽሓፍ ነው

ማለት እንነበባለን ስለዚህ መልካም ምሳሌ እንድንሆን  የተሰጠንን ስራ በታማኝነት እንስራ፣ ጊዜያችንንና ፈቃዳችንን እንሰዋለት፣ እግዚአብሔር በፍሬ እስኪባርከን።

8. በእግዚአብሔር ስራ ላይ መተባበር

ራሱን የቻለ ከመድረክ ያለፈ አገልግሎት ነው። ከትችትና ስራ ከፈታ አእምሮ ይጠብቀናል። አንድ የእግዚአብሔር ሰው ሲናገሩ እንዲህ አሉ "ስራ የፈታ አእምሮ የሃጢያት ቢሮ ነው" ብለዋል።

9. የሌሎች ሙላትና ጉድለት ብቻ የሚታየን ከሆነ

አደጋ ላይ ነን ያለነው ምክንያቱም የተፈተነውን ራሳችንን ለክርስቶስ ለማቅረብ መትጋት እንዳለብን ተጽፎልናል(2ኛ ጢሞ 2፤15) የራሳችንን ሳንወጣ የሌሎችን የምናይበት ትርፍ ጊዜ ያለን አይመስለኝም። እዚህ ላይ ግን ልጨምርበት የምፈለግው ሰውን ከስህተቱ የመመለስ ሃላፊነት፣ ደካማውን የምንሸክምበት ጀርባ የለንም ማለት አይደለም ግን ስለዚህ ነገር የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል? (ገላትያ 6÷ 1-3) በሌሎች ህይወት ላይ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንኑር።

10. ህይወት ይበዛ ዘንድ

በትክክለኛውም መሰረት መታነጽ እንዲሆን  በኛ አመለካከትና እይታ አማኞችን የአገልጋዮች ደቀመዝሙር ሳይሆን  እየሱስ ክርስቶስን እያሳየን የእየሱስ የክርስቶስ ደቀመዝሙር በማድረግ እንትጋ  ።

በመጨረሻም ለማለት የምወደው አንዱን ለመገንባት ሌላውን ማፍረስ የለብንም። አንዱን ስንገነባ ሌላውን ስናፈርስ ዛሬ በብዙ ፍርስራሾች ስለለን እናስተውል ለማለት እወዳለሁ።

## ስለ እግዚአብሔር ሴቶች ምን ያውቃሉ?

- እግዚአብሔር አለማትን  ሲፈጥር መልካም ነው ነው ያለው ግን እግጅ መልካም ነው ነው ያለው ሄዋንን ከፈጠረ በኋላ ነው

- አዳምን ያየነው እንደሆነ በኤደን ገነት ሁሉ በሞላበት ተቀምጦ አካባቢው ሙሉ ደስታ አልሰጠውም ሔዋን ስትመጣ ግን የሚታየው ሁሉ ህይወት ሰጠው

- አዳም በገነት ውስጥ ያሉት አበባዎች አስደንቀውትና ትርጉም ሰጥተውት አያውቁም ልክ ሔዋን ስትመጣ ግን እየቀጠፈ ሲሰጣት ጽጌሬዳ አበባ ትርጉም አገኘ

- አዳም   ጨረቃና ከዋክብትን አድንቆ አያውቅም እንደውም የሚተኛው በጊዜ ነው ሔዋን ስትመጣ ግን አየሽ የጸሓይ፣ የጨረቃና የከዋክብት ውበት ያንቺ አይኖች ግን ከከዋክብቱ ይበልጣሉ እያለ ማድነቅ የጀመረው ሔዋን ከመጣች በኋላ ነው

- ጌታ እየሱስ በምድር ሲመላለስ በገንዘብ ያገለግሉ የነበሩት ዮሃና ሶስናና መግደላዊት ማርያም ነበሩ የወንዶች ስም ግን አልተጠቀሰም

- ሴቶች እግዚአብሔር የሚጠነቀቅላቸው ውድ ልጆቹ ናቸው ጠላት የሆነውን ህዝብ እንኳን አሳልፎ ሲሰጣቸው ወንዶቹን ግደሉ ሲል ሴቶችንና ህጻናትን አትንኩ ነው ያለው

- ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ሴት ከሆነች ከማርያም ተወለደ

- ጌታ እየሱስ ሶስት ጊዜ ሽቱ ተቀብቷል

- ሽቶ በራሱ ላይ ያደረገች ሴት

- ሽቱን በእግሩ ላይ አፍስሳ በጸጉሯ ያበሰችው ሴት

- ጴጥሮስ ባለ ትዳር ነበር በየትም ስፍራ ሚስቱ አብራው ትገኝ ነበር ሓውርያው ጳውሎስ እንኳን ሚስታችንን ይዘን የማንዞረው እኔና በርናባስ ብቻ ነን ወይ? ብሏል

- ጌታ እየሱስ ክርስቶስም በትዳር ውስጥ በሆነው አለት ላይ ነው ቤተክርስቲያንን የመሰረተው

- ጌታ እየሱስ ሊገደል ሲያዝ ሁሉም ሲፈርዱበት ይህ ሰው ጻድቅ ነው በዚህ ሰው ላይ አንዳች አታድርጉ ያለች የጲላጦስ ሚስት ሴት ነበረች

- ወደ መቃብር ሲሄድ እያለቀሱ የተከተሉት ሴቶች ነበሩ

- አስከሬኑን ሽቱና ከርቤ እንቀባ ያሉት ሴቶች ነበሩ

- በጣም የሚገርመው እየሱስ ክርስቶስ ከመቃብር ከተነሳ በኋላ በጣም ለሚቀርቡት ለዮሃንስ፣ ለማቲዎስና ለጴጥሮስ ሳይታይ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው ለሴት ነበር

**"ውሃ ለመነ ወተት ሰጠችው" በሚል ርዕስ በዶ/ር ወዳጄነህ መህረነ ከተሰጠ ትምህርት (ከሲዲ) የተሰወደ**

## አስተያየት

በዚህ  አጋጣሚ ይህን ትምህርት ያዘጋጀውን ዶ/ር ወዳጄነህን እግዚአብሔር ይባርክህ ልል እወዳለሁ። ደግሞም ይህን መጽሔት ለምታነቡ እህቶች ሁሉ ይህን ሲዲ ፈልጋችሁ እንድትሰሙት አበረታታለሁ ምክንያቱም ዘመኑን የዋጀ ትምህርት ስለሆነና በእውነትም እየሆነ ስላለ ነው እንጂ ሴት ስለሆንኩና ስለ ሴት ስላስተማረም እንዳይለደም ለመናገር እወዳለሁ።

ከመልዕክቱ ጥቅል ሃሳቡን ለትምህርት እንዲሆን ሁለት ነጥብ ልተውላችሁ -

አንደኛ ዲቦራ ሁልጊዜ ከአንድ ዛፍ ስር ትቀመጥ ነበር ሁልጊዜ ከመቀመጧም የተነሳ ዛፉ የዲቦራ ዛፍ ተባለ። በጣም የሚገርመው ዲቦራ ተፈላጊ ነበረች ብዙ ጸጋ ነበራት ግን ከዛፉ አትንቀሳቀስም ሰዎችም ወደ እሷ ይመጡ ነበር።

ዛሬ እግዚአብሔር ባስቀመጣችሁ ስፍራ ተቀመጡ ከእግዚአብሔር ጋር እግዚአብሔር ካስቀመጠው ስር በመሆን በታማኝነት አገልግሉ የእናንተ የሆነው ሁሉ በአድራሻችሁ ወደ እናንተ ይመጣል ለእናንተ የታሰበውን ማንም ሊወስደው አይችልም ወዲያ ወዲህ አትበሉ ተረጋጉ፤ ዕረፉ የሚል ሲሆን

ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ እያኤል በሲሳራ ላይ ስላደረገችው ነበር ሲሳራ ጨካኝና የእግዚአብሔርን ህዝብ ያስጨነቀ ነበር ግን በሽሽት ወደ እያኤል ሲገባ ያላት ውሃ ስጭኝ ነበር እሷ ግን ወተት ሰጠችው መጎናጸፊያም ደርባ አስተኛችው ከተኛም በኋላ በጆሮ ግንዱ ላይ ካስማውን በመዶሻ ቸንክራ ገደለችው። ወንድማችን ሲናገር ዛሬም የእግዚአብሔር ሰዎች አስጨናቂዎችን ወተት ጠጥተው መጎናጸፊያ ደርበው የተኙትን የሚገልጡ የጠላትን ስራ የሚያጋልጡና የሚዋጉ እህቶች ይነሳሉ የሚል ነበር።

እያኤል ወተት ስትሰጠውና መጎናጸፊያን ስትደርብ ምህረትን እናያለን በመጨረሻም ስትገድለው እውነትን እናያለን ስለዚህ ምህረትና እውነት አብረውም እንደሚሄዱ በዚሁ ትምህርት ላይ ተጠቃሏል።

# እግዚአብሔርን ማገልገል

በዚህ ርዕስ ላይ ለመጻፍ ስነሳ ሶስት ነገሮችን እንደ አስብ አደረገኝ

1ኛ ማንን ነው የማገለግለው?
2ኛ ለማገልገል በውስጣችን ያለውን ስጦታ ማነሳሳት
3ኛ ለማገልገል ትጋት አለኝ ወይ?

በመሰረቱ እግዚአብሔር ሰውን ለማገልገል ሲጠራ ማንነቱን ያሳውቃል ታዳጊነቱን ያሳያል ፍቅሩን ይገልጻል። በመጀመሪያ የጠራቸውን የእስራኢልን ህዝብ እንዴት እንደታደጋቸው በሙሴ አማካኝነት እንመልከት "…እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እንዲያገለግለኝ ህዝቤን ልቀቅ ዘዳ 8፤20" እግዚአብሔር የእስራኤልን ህዝብ እንዲያገለግሉት ሲጠራቸው በባርነት ቀንበር ስር እያሉ መከራቸው በበዛበት መብት በሌላቸው ጊዜና የራሳቸው ፈቃድ ባልነበራቸው ጊዜ እግዚአብሔር የዝቡን መከራ ተመለከተ ታላላቅ ድንቅና ታምራትን በማድረግ ህዝቡን ከባርነት ነጻ ሲያወጣ እንመለከታለን ነጻ የወጣ ሰው ብቻ ነው እግዚአብሔርን ማገልገል የሚችለው ዛሬ እኔና እናንተ በሚበልጠው ቃል ኪዳን በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ ከዓለም ከአለው ጥፋት አምልጠን ከመለኮት ባህሪይ ተካፋይ ሆነን የእግዚአብሔርን በጎነት መልካምነት አዳኝነት ለመናገር ለዚህ አገልግሎት ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን አመጣን።

**በአንደኛ ደረጃ** ማንን ነው የምናገለግለው? በቆላ 3፤23 "ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት ከጌታ የርስቱ ብድራትን እንደምትቀበሉ ታውቃላችሁና የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስን ነው"

ማንን ነው የምናገለግለው በዚህ ጥቅስ መሰረት የምናገለግለው ጌታ እግዚአብሔርን ነው ይኸ የገባው ሰው ሲያገለግል ለሰው ለመታየት ለእይታ ሳይሆን ለአምላካችን ክብር ማገልገል አለበት ብድራትን የምንቀበለው ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነው ስለዚህ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ እንጂ የሰው አይደለችም ይኸንን በደንብ ከተረዳን ለማገልገል አንቸገርም በምናገለግልበት ቦታ ላይ እግዚአብሔር ሃይሉን በመግለጽ ከክብር ወደ ክብር ያሻግረናል።

**በሁለተኛ ደረጃ** ለማገልገል በውስጣችን ያለው ስጦታ ማነሳሳት ያስፈልጋል 2ኛ ጢሞ 1፤6 "ስለዚህ ምክንያት እሳት እንደሚቀጣጠል ሰው እጆቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሳሳ አሳስበላሁ"እግዚአብሔር በመንፈሱ አማካኝነት ለእያንዳንዱ አማኝ ጌታን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ስጦታን ተቀብሏል ስለዚህ በውስጣችን ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ልናነሳሳ ያስፈልገናል።

እግዚአብሔር ለአገልሎት ሲጠራን ያለስጦታ በራሳችን እንድናደርገው ምንም ነገር አያዘንም እግዚአብሔር የሚፈለገን መሳሪያ እንድንሆነው ነው ስለዚህ በውስጣችን ያለውን ስጦታ ማነሳሳት አለብን ሁለተኛ ካላገለገልን እድገት የለም የሚያገለግል ሰው እንደሚወርድ ወንዝ በየጊዜው በአዲስ ነገር ራሱን ያድሳል ዝም ብሎ የተቀመጠ የማያገለግል ሰው እንደረጋ ውሃ ይመስላል በውስጡ ያለውን ካላካፈለ ካልተጠቀመበት ማደግ የለም በቤቱ የዳነብትን ቀን መቁጠር ብቻ ይሆናል ማለት ነው ስለዚህ ቤተክርስቲያን በከፈተችለት በር ሁሉ ልናገለግል ያስፈልጋል።

**በሶስተኛ ደረጃ** አገልግሎት ትጋትን ይጠይቃል በሮሜ 12፤11 "…ለስራ ከምታጋት አትለግሙ" ይኸ የሚያሳየን አገልጋይም ሆኖ የሚለግም አለ ማለት ነው ስለዚህ እግዚአብሔርን ማገልገል በገንዘብ ተምንነው ብዙ ከተከፈለኝ በትጋት እሰራለሁ የምንለውም ጉዳይ አይደለም ወደ እግዚአብሔር መንግስት የገባነው በስራ ሳይሆን በእምነት ነው። ስለዚህ የምንሰራው ለአመነው ነገር እንጂ በገንዘብ ለሚተመን ጉዳይም አይደለም ስለዚህ አገልጋይ አምላኩን ታምኖ በንጹህ ልብና በንጹህ ህሊና ለጌታ ራሳችንን በመስጠት ልናገለግለው ይገባናል።

በዚህ ጽሁፍ ላይ መግለጽ የምፈልገው ሰው በልቡ እግዚአብሔርን ለማገልገል መፈለግ አለበት እኔና እናንተ እንደዳንበት መዳን እግዚአብሔር ሊሎችንም ሊያድን ይፈልጋል ለዚህም መሳሪያው ሰው ነው የመረጠውም መላዕክት በምድር እንዲያገለግሉ አይደለም የመረጠው በክርስቶስ የዳነውን ሁሉ ነው ስለዚህ በዋጋ ተገዝታችኋል ከዚህ በኋላ የራሳችሁ አይደላችሁም ላለማገልገል ምክንያት የለንም በተሰጠን ሁላችን ስናገለግል የክርስቶስን አካል ሙሉ እናደርጋታለን ድነን የኔና የናተ አለማገልገል የቤተክርስቲያንን ሙላት ያጎድላልና።

ለማጠቃለያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔርን የሚያገልግል ሰው ዘካሪያስ የሚባል ባለቤቱም ኤልሳቤጥ የምትባል ሁለቱም በጌታ ትዕዛዝና ህግጋት ሁሉ ያለነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ ነገር ግን በህይወታቸው የጎደለ ነገር ልጅ አለመውለዳቸው ጥያቄ ነበራቸው ሆኖም ጥያቄ አለንና እግዚአብሔርን አላገለግልም አላለም እንደዚያም ሆኖ ፍጹም በሆነ ታማኝነት ወደ ጌታ ቤተመቅደስ ገብቶ ለማጠን ዕጣ ደርሶበት ሳለ ለማገልገል በገባበት ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦለት የዘመናት ጥያቄው ሲመለስ የተሰጠውም ልጅ የጌታን መንገድ የሚጠርግ ጌታም እንደመሰከረለት ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሃንስ የሚበልጥ ማንም የለም ዛሬም ለኔና ለናንተ ጥያቄ ቢኖረን ጌታን ታምነን በታማኝነት ብናገለግለው ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለትውልድ መትረፍ የምንችልበትን በረከት ያፈስልናል። ወገኖቼ እግዚአብሔርን ማገልገል ማትረፊያችን ነው።

ጌታን በማገልገል ተባረኩ

ከዘነብ አሰፋ

# እየሱስ ለእኔም መልካም ነው



“በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሔድ
አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም” መዝሙር 22፤4

ይህንን የምስክርነት ቃል ለምታነቡ እህቶቼና ወንድሞቼ ሁሉ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ ይህ ያለፈው ዓመት 2007 ማለት ነው አጀማመሩ ለኔ መልካም አልነበረም ነገር ግን ፍጻሜውን እግዚአብሔር መልካም አደረገው በማርች/2007 በድንገት ታመምኩኝ ከመኝታዬ መነሳት እስከሚያቅተኝ ድረስ ቃተትኩኝ ተነስቼም ለመሄድ ስሞክር አቅምና ጉልበት ፈጽመው ከዱኝ ለመጀመሪያ ጌዜ በህይወቴ ተሰባሪ መሆኔን ተገነዘብኩኝ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለሁ በሴንትፖል አካባቢ በሚገኘው የቅዱስ ዮሴፍ የህክምና ማዕከል ምርመራ መከታተል ጀመርኩኝ ነገር ግን የበሽታዬ መንስኤው ምን እንደሆነ ለማወቅ በጣም ተሳናቸው እኔም ከዕለት ወደ ዕለት ህመሙ እየጠነከረብኝ ስራ መሄድ ሁሉ አቃተኝ ጉልበቴም ደከመ ልቤም ከሚገባው በላይ መምታት ጀመረ እንቅልፍ ሳልተኛ ያደርኩባቸውን ቀናቶች መቁጠር እንኳን ተሳነኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቸኝነት ተሰማኝ ተስፋ መቁረጥም ይታይብኝ ነበር በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን የእየሱስን ስም ከመጥራት አላቋረጥኩኝም ነበር ጠዋት ስነሳ፤ ማታም ስተኛ አንተ ልትፈውሰኝ ይቻልሃልና እያልኩ ማልቀስ ጀመርኩኝ በእርግጥም ሞት በራፌ ላይ እንደሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ ተገነዘብኩኝ ከፍርሃትም የተነሳ የምኖርበትን ቤት (Aprtment) በሩን ክፍቱን ማሳደር ጀመርኩኝ ድንገት ብሞት እንኳ ለአካባቢው ሁኔታውን ለማመቻቸትና አስክሬኔን በማሽተት ችግር እንዳይፈጥር ለማመቻቸት ማሰቤ ነበር በዚህ ሁኔታ ወሩ ተጠናቆ ወደ ኤፕሪል ተሸጋገርኩኝ ቢሆንም ከሃኪሞቹ ዘንድ አንዳችም ምላሽ አላገኘሁም በመጨረሻም ህመምህ ምን እንደሆነ ማወቅ አልቻልኩም በጣም ሙሉ ጤነኛ ነህ ስለዚህ በኛ በኩል የምንረዳህ ነገር የለም በማለት አሰናበቱኝ ሁኔታዬን በቅርብ ይከታተል የነበረ ወንድሜና ጓደኛዬ የሆነ ሰው በሮቸስተር ከተማ በሚገኘው የሜዩ (Mayo Clinic) በህክምና ስለሚሰራ ሊረዳኝ በሚችለው ሁሉ ጥረት በማድረግ ወደ እርሱ ዘንድ በአስቸኳይ እንድመጣ አደረገኝ ከዚህ ሆስፒታል እንደደረስኩኝ በአፋጣኝ መድከሜን ስለተገነዘቡ ተሯርጠው እንድተኛ ተደረገ ሌሊቱንም ደም ከተሰጠኝ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ  ያጣሁትን እንቅልፍ ተኝቼ አደርኩ፡፡

በነጋታውም አስፈላጊው ምርመራ ከተከናወነ በኋላ ሓኪሞቹ ተሰብስበው ወደ ክፍሌ በመምጣት ህመሜ ምን እንደሆነ ገለጹሉኝ፡፡ የደም ካንሰር ስለሆነ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን በማለት አስረድተውኝ ከክፍሌ ወጡ ለጊዜው በአጠገቤ ማንም አልነበረምና በሃዘን ተዋጥኩኝ፤ ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህ ዓለም ከንቱ መሆኑንና በእንግድነት እንዳለሁ ተገነዘብኩኝ ህይወት አጭር መሆኗንም አወኩኝ ለካስ ይኸው ነው አልኩኝ ለራሴ፡፡ የማምነው እግዚአብሔርስ የት ነው ያለው ብዬ መጠየቅ ጀመርኩኝ፡፡ አዎ ጌታ አንተ ከኔ ጋር ነህ በእውነትም ከዚህም በሽታ አንተ መፈወስ ትችላለህ በማለት ወደ አምላኬ ተማጠንኩኝ፡፡ እንባዬም አጥብቆ ይፈስ ነበርና በአጠገቤ የነበሩት ነርሶች ሊያበረታቱኝ ሞከሩ፤ ፤ ግን ሁሉም ከንቱ እንደነበርና እኔም በዚህ ዓለም ያለኝን እንግድነት ወደ ማጠናቀቁ መሆኔን በመረዳት እራሴን ለማጽናናት ሞከርኩኝ፡፡ ጊዜውና ሁኔታው አመች አልነበረም፡፡ ህክምናውም ተጀመረ፡፡ ብዙም ከመጎሳቆሌም በላይ ተስፋ እስከማጣት ደረስኩኝ፡፡ ልመናዬና ጸሎቴ ግን አልተቋረጠም ነበር፡፡ አጥብቄም ለመንኩት፡፡ አዎ አንተ ይቅር ባይ አምላክ ነህና እባክህን ጎብኘኝ አልኩት፡፡ ለመጀመሪያም ጊዜም የማውቀውም መሰለኝ፡፡ አዎ በቤትህ ብዙ  ተመላልሻለሁ ነገር ግን አንተ የምትፈልግብኝን ያህል ባልሆንም በዚህ እንደማትቀጣኝ አምናለሁና መልካምነትህን አሳየኝ በማለት አለቀስኩኝ፡፡ በእውነትም የሚሰማ አምላክ ነው ያለኝ፡፡ ለእኔም መልካም ሆነ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ ብዙዎቻችሁ ከአጠገቤ አልተለያችሁኝም፡፡ ሁላችሁም ለእኔ ጸልያችኋል፤ ለእኔ ተማጽናችኋል፤ አልቅሳችኋል፡፡ ጌታ ግን ቅርብ ነበር፡፡ የእያንዳንዳችሁን ጸሎትና ልመና ተቀበለ፡፡ ከሰባት የጭንቅ ወራቶች በኋላ እንደገና የመኖር ተስፋ አየሁኝ፡፡ ከህመሜ ፈጽሞ ተፈውሼ ከሆስፒታል ወጣሁኝ፡፡ እኔን በጣም ያስደነቀኝ መታመሜ አልነበረም፡፡ ከሁሉ በላይ ያስደነቀኝ የአመንኩት ጌታዬ ለኔ መድረሱና መገኘቱ ነበር፡፡ እሱ ብርሃኔና መድሃኒቴ እንደሆነ አጥብቄ ተረዳሁኝ፤ ፤ ሁሉ ከንቱ እንደሆነም ተገነዝብኩኝ፡፡ መልካምነቱንም ለዘላአለም አወራለሁ እሱ ለእኔ መልካም ነውና፡፡
እኔ እድል አጋጥሞኝ በታወቀ ሆስፒታልና በዓለም በታወቁ የህክምና ባለሙያዎች ብርታት አልተረፍኩኝም ከዚህ በሽታ ፈጽሜ የዳንኩት ዘላለማዊ የሆነው አምላኬ ስለደረሰልኝ ብቻ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች በዚሁ ሆስፒታል ውስጥ እኔ ያገኘሁትን ዕድል አላገኙም፡፡ ብዙዎች ሲያልፉ ተመልክቻለሁኝ፡፡

በጌታ የምወዳችሁ ወገኖቼ ሁሉ ላስገነዘባችሁ የምወደው ነገር ቢኖር ይህች ዓለም ከንቱ ናትና በጌታ ሆናችሁ ብትቆዩ መልካም ነው እላለሁ፤ ፤ ዛሬ ዓለም በተናወጠበት ሰዓት የእየሱስ ክርስቶስ መምጫው ሰዓት አይታወቅም፡፡ ሞትም እንደዚሁ ነው፡፡ ህይወታችን እንደሚሰበር ብርጭቆ መሆኑን ከተገነዘባችሁ አጥብቃችሁ በጸሎት ተጠባበቁ፤ ፤ ጌታን አጥብቃችሁ ፈልጉት፡፡ ስለነገ ብዙም አትጨነቁ የነገውን የሚያውቅ አምላካችን ብቻ ነው፡፡ “ለማንም ሰው በክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ፡፡ ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ”፡፡ ሮሜ 12፤17-19

ይህንን ነው ላስገነዝባችሁ የምወደው፡፡ የሰው ልጅ ጥላችንና ምሬትን ይዞ ወደ ሞት ሲሄድ ያሳዝነኛል፡፡ የማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፡፡ ዕዳ ስል “የጥላቻ” ዕዳ ማለቴ ነው፡፡ በፍቅር ተመላለሱ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስረዳን “ፍቅር ይታገሳል፤ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ አመጻ ደስ አይለውም ሁሉን ይታገሳል፤ ሁሉን ያምናል፤ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፤ በሁሉ ይጸናል” ቆሮንቶስ 13፤ 4-7 ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ዛሬም በዙፋኑ ላይ ታቀምጦ ይፈውሳል፡፡ የዳንኤል፤ ፤ የአብርሃም፤ የይስሃቅ፤ የያዕቆብ፤ የዮሴፍ እንዲሁም የኔ አምላክ ዛሬም ይሰራል፤ ያድናል፤ ይባርካል፤ እኔ ለዚህ በቂ ምስክር ነኝ፡፡

ብዙ የታመሙ ሲፈወሱ አይተናል፡፡ መውለድ ያቃታቸው ሲወልዱ አይተናል፡፡ የተቸገሩ ከችግራቸው ተፈተዋል፡፡ እያንዳንዳችሁ የምታልፉበትን ሁኔታ ባላውቅም ለኔ መልካም የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእናንተም በተቸገራችሁበትና በደከማችሁበት ነገር ላይ ጌታ መልካም እንደሚያደርግ ሳረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡ ተስፋችን እሱ ብቻ ስለነሆነ በተስፋ እንጠብቅ፡፡

ስለዚህ ይህን ነው ልተውላችሁ የምወደው፡፡ የማምነውና የማፈቅረው አምላካችን እናንተንም ያስባችሁ፡፡ ለእኔ መልካም እንደሆነ ለእናንተም መልካም ይሁንልላችሁ፡፡ በዚች ምድር ላይ የምንኖረው በጣም ለአጭር ጊዜ ስለሆነ እርስ በርሳችን ልንፈላለግ፤ ልንረዳዳ፤ ልንደጋገፍ ይገባናል፤ ፤ አንዳችን ለአንዳችን መድሃኒት ስለሆንን በፍቅር እንተሳሰብ፡፡ እኔ ያለ እናንተ እናንተም ያለ እኔ መንገዱ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ በህመም በወደኩበት ሰዓት ላሳያችሁኝ ፍቅር፤ በጸሎታችሁ፤ በገንዘባችሁ ያለመሰልቸት ለጎበኛችሁኝና ላሰባችሁኝ ሁሉ እግዚአብሔር ጸጋውን ያብዛላችሁ፡፡ ተስፋችን የሆነው ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ቅርብ ነውና አጥብቃችሁ ጸልዩ፡፡ ከእናንተ ወገን ሆኜ ጌታዬን ስለማመልከው ጸጋውን አብዝቶልኛልና ለእናንተም ጸጋውን ያብዛላችሁ፡፡ በጣም እወዳችኋለሁ፡፡ ጌታ እየሱስ ይጠብቃችሁ፡፡

ከጌታቸው ተክሉ

# ወርቃማ ቃል

"ልጄ ሆይ ስማ ጠቢብም ሁን
ልብህንም በቀናው መንገድ ምራ
የወይን ጠጅ ከሚጠጡ ጋር አትቀመጥ
ለስጋም ከሚሳሱ ጋር
ሰካርና ሆዳም ይደኸያሉና
የእንቅልፍም ብዛት የተቦጫጨቀ ጨርቅ
ያስለብሳልና"
ምሳሌ 23፤19-21

"ዋይታ ለማን ነው? ኃዘን ለማን ነው?
ጠብ ለማን ነው? ጩኸት ለማን ነው?
ያለ ምክንያት መቁሰል ለማን ነው?
የዓይን ቅላት ለማን ነው?
የወይን ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ
አይደለምን?
የተደባለቀ የወይንን ጠጅ ይፈትኑ ዘንድ
ለሚከተሉ አይደለምን?
ወደ ወይን ጠጅ አትመልከት
በቀላ ጊዜ መልኩም በብርሌ ባንጸባረቀ ጊዜ
እየጣፈጠም በገባ ጊዜ
በኋላ እንደ እባብ ይነድፋል
እንደ እፉኝትም መርዙን ያፈስሳል"
ምሳሌ 23፤29-32

# መዝሙረ ቴሌቪዥን

ቴሌቪዥን እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝም የለም
በሶፋ ላይ ያሳድረኛል በክፉ መንገድ ይመራኛል
ነፍሴን አባከናት በብራታቱም በራሱ መንገድ መራኝ
በቤተሰብ ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ
ቲቪ ከኔ ጋር ነውና ምክር አልፈልግም
ዘፈኖቹና ፊልሞቹ እነሱ ያጽናኑኛል
በፊቴ ሃጢያትን አዘጋጀልኝ
በሁሉም ፊት ለፊት ራሴን በባዶነት ሞላው
ስንፍናና ክንቱነት በህይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል
በቤቴም ቴሌቪዥን እያየሁ ሁልጊዜ እኖራለሁ

(ከአዲስ አበባ የህይወት መጽሔት ጋዜጣ የተወሰደ)

"ጻድቅ የሚድነው በጭንቅ ከሆነ..."
1ጴጥ 4፤18

ከእግዚአብሔር ከአብ ከአዳኛችንም ከክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋና ሰላም ለሁላችን ይሁን፡፡

በዚህ ባለንበት ዘመን እግዚአብሔርን ፈርተንና አውቀን ልንኖር ለሚገባን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳችን የምስራች እንኳን ደስ ያላችሁ ይለናል፡፡ ምክንያቱም ስንጠየቅ መልሱ "እየሱስ ይመጣል፤ ማራናታ" በሚል ሁለት ድንቅ ቃሎች ያጽናናናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችን በብዙ ቦታ ስለ ዘመኑ ሲናገር ቀኖቹ እጅግ ክፉዎች እንደሆኑ (ኤፌ 5፤16) ትውልዱ ጠማማና ክፉ እንደሆነ (ፊል 2፤15) ጌታ ኢየሱስም በማርቆስ 8፤38 ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ትውልዱ ዘማዊና ኋጢያተኛ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ እንግዲህ እነዚህን ቃሎችና ሌሎችን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ስንመለከት ያለንበት ዘመን ይህንኑ የሚያመለክት እንደሆነ በግልጽና በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡ አንድ ማስተዋል ያለብን ነገር መጽሐፍ ቅዱሳችን ከተጻፈ ብዙ ዘመናት የተቆጠሩ ቢሆንም በተጻፈበት ዘመን ግን ትውልዱ ክፉ፤ ጠማማ፤ ዘማዊ፤ አመንዝራ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ታዲያ በዛ ዘመን ትውልዱ እንዲህ ከተባለ ዛሬ ያለንበት ትውልድ ምን ሊባል ወይንም ምን ዓይነት ስም ልናወጣለት እንችል ይሆን? ዛሬ ግን በዚህ አጭር መልእክቴ ለዚህ ትውልድ መፍትሔ የሚሆንን ነገር አቀርባለሁ፡፡ ይኸ መፍትሄ የተወሰደው ከሁሉ በላይ ከሆነው፤ ከእግዚአብሔርና መንፈስ ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ብዙዎች አምልጠውበታል ደግሞም ብዙዎች ይህንን መፍትሄ ባለመቀበላቸው የዘላለም ፍርድ እየጠበቃቸው ይገኛሉ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ስለትውልዱ አስፈሪነት ተናግሮ ያለ መፍትሔ አልተወነም፡፡ ነገር ግን እንዴት ልንመላለስ እንደሚገባ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡

የእግዚአብሔር ቃል በሉቃስ 3፤4-6 እንደሚናገር ሁላችን የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስን ጸጋና መንፈስ የተቀበልን "ድምጽ" ልንሆን ይገባል

ይህም ድምጽ ሰዎች የጌታን መንገድ እንዲያዘጋጁ ጠማማው ጎዳናም እንዲቀና ሸካራውም ጎዳና ትክክል እንዲሆን ማሰማት አለበት፡፡ ስለ መጥምቁ ዮሓንስ መጽሓፍ ቅዱስ ሲናገር "በበረሃ የሚጮህ ድምጽ" ይላል፡፡

አዎ እኛም ምንም ዙሪያችን የሚሰማ ነገር በሌለ በሚመስልበት ቦታ ሁሉ ወይንም ምድረ በዳ በሆነ በሚመስል ቦታ ላይ ይህንን ድምጽ ጮክ ብለን ማሰማት አለብን ብዬ እመክራለሁ፡፡ ይኸው የእግዚአብሔር መንፈስ አገልጋይ የሆነው መጥምቁ ዮሓንስ በሉቃስ 3፡18 እንደሚናገር ራሳችንና ሕዝባችንን በብዙ የምክር ቃላት ህዝቡን እያስጠነቀቅን ወንጌልን ልንሰብክ አስፈላጊ መሆኑን ዘመኑን በማየት መረዳት ይቻላል፡፡ ጌታ ለአንድ ነፍስ እንኳ ቢሆን ዳግመኛ መምጣቱ እንደሚዘገይ እናስተውል!

በመልዕክቴ መጀመሪያ የጠቀስኩት የእግዚአብሔር ቃል እውነተኛና የማይሻር መሆኑን ሁላችን እንድናስተውል የልብ ጸሎቴ ነው፡፡ "ጻድቅ የሚድነው በጭንቅ ከሆነ" ጻድቅ በጸሎት አይድንም፣ ጻድቅ በተድላ አይድንም፣ ጻድቅ ተኝቶ አይድንም፣ ጻድቅ እሁድ ቤተክርስቲያን በመምጣት አይድንም፡፡ ነገር ግን ጻድቅ በዚህ ክፉና ጠማማ በሆነ ትውልድ መሓከል ሲኖር በጭንቅ ይድናል፡፡

ለመሆኑ ጻድቅ ማነው? በዚህ ምድር ላይ ጻድቅ አለ ወይ? ብለን ብንጠይቅ መልሱ አዎን ነው፡፡ ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ህግን ሳይሆን የኢየሱስን ጸጋን በመቀበል ጻድቅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገር በሮሜ 3፡28፣ በገላቲያ 2፡16 እና በሌሎችም ስፍራዎች በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ መገኘት የሚቻለው በክርስቶስ እየሱስ የተሰራውን የመስቀሉን ስራና ትንሳኤውን በማመን ብቻ ነው፡፡ ወደዚህ እምነት ያልመጣችሁ ሁሉ ይህንን ድምጽ ሰምታችሁ ለጌታ ዳግም ምጽአት ራሳችሁን ሙሽራ አድርጋችሁ እንድትዘጋጁ በጌታ በኢየሱስ እንለምናችኋለን፡፡

ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ለምን "ጻድቅ በጭንቅ ይድናል" አለ? ብለን ልንጠይቅ እንችላለን፡፡ ለዚህም መልስ ይሆነን ዘንድ 1ኛ ጴጥሮስ 4 እና 2ኛ ጺጥሮስ 2 ልናነብና ልናጠና እንችላለን፡፡ ይህ ቃል ሎጥ የነበረበትን ዘመን እያስታወሰን ሎጥ በነበረበት ዘመን እንዴት በጭንቅ ይኖር እንደነበር ይናገራል፡፡ ሎጥ አመጸኛና ሴሰኛ በሆነ ትውልድ መካከል ይኖር እንደነበር በሚያየውና በሚሰማው ነገር ነፍሱ ዕለት ዕለት በአመጸኛ ድርጊታቸው ትጨነቅ እንደነበረ እያወሳ ዛሬም እኛ በዙሪያችን ያለውን ነገር ስናይና ስንሰማ እንዴት መመላለስ እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ይናገራል፡፡

ወገኖቼ ለሆናችሁና በጌታ ለጸደቃችሁ ሁሉ አንድ መልዕክት አለኝ በገላቲያ 6፡7 ላይ እንደተጠቀሰ "እንታለል እግዚአብሔር አይዘበትበትም" እግዚአብሔር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተዘብቶበታል፣ ፣ መቼ ልትሉ ይሆናል፡፡ ጌታ እየሱስ ራሱን አሳልፎ በሰጣት በዚያች ሌሊት ተዘበተበት፣ ታፊዘበት፣ ተተፋበት፣ ተገረፈ፣ ተሰቀለ፣ ሞተ፣ ተነሳም፡፡ ከዚህ በኋላ ግን የሰው ድርሻ ቀርቷል፡፡ የኛም ድርሻ ይህንን ኢየሱስ ማምለክና ለእርሱ መኖር፣ ስለ እርሱ ማሰብ፣ እርሱን መልበስ፣ በእርሱ መበርታት፣ ስለ እርሱ ማውራት ሊሆን ይገባል፡፡

ሰው ሁሉ እንደ ስራው በፍርድ ቀን ድርሻውን ያገኛል፡፡ ስለዚህ በዚህ ምድር ላይ ስንኖር በጥንቃቄ፣ የስጋችንና የዓለምን ምኞት በመንፈስ በመግደል መሆን አለበት፡፡ ያን ክቡር ጸጋ ከንቱ እንዳናረገው ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡ የሚያጣፍጥ ጨውና ብርሃን ተብለን በክርስቶስ የክብር ቦታ ተሰጥቶን መራራና ጨለማ ሆነን በፊቱ እንዳንገኝ "ዛሬ" እየተባለ በሚጠራበት በዚህ ቀን እራሳችንን ልንመረምር ይገባል፡፡

እናስተውል! በዚህች አገር ውስጥ (በአሜሪካ) ለመኖር እግዚአብሔር ዕድልንና መንገድን የከፈተልን በዙሪያችን ያለውን ነገር "ሁሉ" እንድንጠቀምበትና እንድንመስለው ሳይሆን ነጻነታችንን ለእግዚአብሔር ክብር ለቤተክርስቲያንና ለምድራችን ደግሞ በረከት እንድንሆን መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ጥያቄው ግን ዛሬ ነጻነቱን ለእግዚአብሔር ክብር የተጠቀመበት ማነው? የሚል ነው፡፡ ይህ እውነት የገባት የጌታችንና የአምላካችን እናት የሆነችው ማርያም በሉቃስ 1፡53 ላይ ስትዘምር "የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአቸዋል፣ ሓብታሞችን ግን ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል፡፡" ዛሬ ታዲያ የተራብነው በጎ ነገር ነው ወይስ ሃብት ነው? መቼስ ሃብት ስል ምን ማለቴ እንደሆነ ይገባችኋል ጌታ ኢየሱስ ሃብትንና ልብን አንድ አድርጎ በማቴ 6፡19-21 አስተምሮአል ልባቸውን በዚህ ምድር ላይ ያደረጉ ሰዎች ምድራዊ ሃብትንና ዕውቀት ብል በሚበላው፣ ዝገት በሚያበላሸው፣ ሌባም ሊሰርቀው በዚህ ምድር ላይ ሃብት ያከማቻሉ፡፡ ስለዚህ ዓይነት ሰው ጌታ በሉቃስ 12፡13-21 ሲናገር "አንተ ሞኝ ነፍስህን በዚህች ሌሊት ከአንተ ሊወስዱ ይፈልጉታል እንግዲህ ለራስህ ያከማቸኸው ለማን ይሆናል? አለው" ይላል አቤት ስንቶቻችን በእግዚአብሔር ፊት ስንታይ ዛሬ "ሞኞች" ተብለናል፡፡ እግዚአብሔር ማስተዋልን ይስጠን፡፡ ለተቃራኒው ደግሞ ሃብታቸውን በላይ በሰማይ የሚያከማቹ፣ ስለሰማያዊ ነገር የሚያስቡ፣ የሚታየውን ሳይሆን የማይታየውን ነገር ላይ ሃሳባቸውንና ልባቸውን ያደረጉ ማርያም እንዳለች በጎ ነገርን ለተራቡ ሁሉ እግዚአብሔር አጥግቧቸዋል፡፡ ያጠግባቸዋል አይልም፡፡ "አጥግቧቸዋል"፡፡ ባላቸው ነገር ረክተው የእግዚአብሔርን አዲስ ህይወት ተስፋ ያደረጉ ሁሉ የአግዚአብሔር ደስታ ይሆናሉ፡፡ እንግዲህ ሓዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 13፡11 እንደሚል ዘመኑን በማስተዋል ይህን አድርጉ፣ ከእንቅልፋችሁ የምትነቁበት ጊዜ አሁን ነው መዳናችን መጀመሪያ ካመንበት ጊዜ ይልቅ አሁን ወደ እኛ ቀርቦአል፡፡ የጨለማን ስራ ጥለን የብርሃንን ጦር ዕቃ እንልበስ፡፡ እንዲሁም በኤፌሶን 5፡11-17 እንደሚል ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን በሚገባ ዋጁ ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ፡፡

ከእነዚህ ከተጠቀሱት ሁለት የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ሁለት ነገርን እንመልከት፡፡ አንደኛው ዘመኑን አስተውሉ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለዘመኑ በሚገባ ህይወት እንመላለስ፡፡ አንደኛውን እስከአሁን በጻፍኩት መልዕክቴ ያስረዳሁ ይመስለኛል፡፡ ዘመኑ ክፉ፣ ጠማማ፣ ሓጢያተኛ፣ አመንዝራ፣ ዘማዊ ሌላም ሌላም፣ ፣ ይህንን ግን ማወቅ ሳይሆን ልናስተውል ይገባል፡፡ ምክንያቱም ያላስተዋልነው ነገር ለአደጋ ይጥለናል፡፡ ደግሞም የሚያስፈልገንን ትጥቅ መያዝ የምንችለው በምን ዓይነት ትውልድ መሓከል እንደምንኖር ስናስተውል ብቻ ነው፡፡ ሁለተኛው በዚህ ዘመን ስንኖር በምን ዓይነት ህይወት መመላለስ እንዳለብን ይነግረናል ይኸውም የጨለማን ስራ እንጣል የብርሃንንም ጦር ዕቃ እንልበስ፣ ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እናስተውል

የጨለማን ስራ እየጣልን የብርሃንን ጦር ዕቃ እንልበስ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ቀድሞ በዚህም ስንኖር እኛ ራሳችን ጨለማ እንደነበርንና አሁን በጌታ በጸጋው ከዳንን በኋላ ብርሃን እንደሆንን በኤፌሶን 5፡8 ላይ ይነግረናል፡፡ ገና ኋጢያተኞች ደካሞችና የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት ከራሱ ጋር ያስታረቀን እግዚአብሔር ለዚህ ለሰጠን ህይወት ከእኛ የሚጠብቀው የህይወት ምላሽ እንዳለ የእግዚአብሔር ቃል በብዙ ስፍራዎች ይናገራል፡፡

ይኸውም የህይወት ምላሽ "እምነት" ይባላል፡፡ እምነት ጌታን ስንቀበልና የህይወታችን አዳኝ ስናደረገው ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን የጽድቅ ህይወትም ለመኖር "እምነት" ዋነኛው የእግዚአብሔር ጥያቄ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ቃል ሮሜ 6 ስንመለከት ሰው ጌታን አዳኝ አድርጎ መንገድን ከጀመረ በኋላ የኃጢያት ባርያ እንዳይሆንና የኋጢያት ሰውነት እንዲሻር አሮጌው ሰው ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀለ ይነግረናል፡፡ እንዲሁም ለኋጢያት ሞተን በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደሆንና ራሳችንን እንደዚሁ አድርገን በ "እምነት" መቁጠር እንዳለብን ይነግረናል፡፡ ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች ዛሬ አሮጌው ሰው እንደተሰቀለ ለእግዚአብሔር ህያዋን እንደሆንን በእምነት መቀበል ስለሚያዳግታቸው ወደ ቀድሞው የጨለማ ህይወት ወይም የኃጢያት ህይወት ሲመለሱ ይታያል፡፡

ነገር ግን ይህን ጽሁፍ ለሚያነቡና ከጨለማ ህይወት መለየት ለከበዳቸው አንድ መልእክት አለኝ አዎን የኃጢያት ባሮች ወይም እራሳችን የጨለማ ህይወት ምሳሌዎች ነበርን፡፡ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ቃል በሙሉ ልብ በመታዘዝ ከኃጢያት ነጻ መውጣት፣ የጽድቅ ባሪያ መሆን ይቻላል፡፡ ከምንም በላይ ከራሳችን የማድረግና ያለማድረግ አቅም በላይ የእግዚአብሔርን ቃል እንመነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እኛን የጽድቅ ባሪያ አድርጎ የቅድስናን ፍሬ እንድናፈራ ሊያረገን ይችላል ብዬ አምናለሁ፣ ፣ እንደ ብርሃን ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ልንኖር ይገባል፣ ፣ የብርሃኑ ፍሬ በበጎነት፣ በጽድቅና በእውነት የሚገለጥ ሲሆን ከጨለማ ስራ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም፡፡

የእግዚአብሔርን ፍቃድ እናስተውል፡፡ “ሞኞች አትሁኑ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አስተውሉ እንጂ”የሚለው የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ የሚነግረን ነገር ቢኖር የእግዚአብሔርን ፈቃድ አለማስተዋል ሞኝነት ነው፡፡ አቤት ስንቶቻችን ሞኞች ሆነን ይሆን? በመክብብ 10፥2-3 ላይ የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሞኝ ሲናገር የሞኝ ልብ ወደ ግራ የጠቢብ ልብ ግን ወደ ቀኝ እንደሆነና ሞኝ በጎዳና ሲሄድ ማስተዋል እንደሚጎድለው በግልጽ ይናገራል፡፡ እንግዲህ አንድን ሰው ሞኝ የሚያስብለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ አለማስተዋሉ፣ ቀኝን ሳይሆን ግራን መምረጡ ነው የእግዚአብሔር ቃል የጌታን ፈቃድ አስተውሉ ብሎ ሲናገር በማስተዋል ውስጥ ያለውን መረዳት ሊያሳስበን ስለፈለገ ነው፡፡

የጌታን ፈቃድ ማወቅና ማስተዋል ልዩነት ያላቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ሰዎች የጌታን ፈቃድ ካወቁት ነገር ግን ካላስተዋሉት ፈቃዱን መፈጸም እንደማይችሉ ቃሉ ይናገራል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል በሮሜ 12 ላይ ሲናገር በጎ መልካምና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ በመጀመሪያ እራሳችንን ለእግዚአብሔር ቅዱስ ህያውና ደስ የሚያሰኝ መሰውዕት አድርገን ልናቀርብና ይህንንም ዓለም እንዳንመስል ያስተምረናል፡፡ ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ፈቃድ ሶስት ነገሮችን ያካትታል፡፡

ሀ. ራስን ከጨለማ ህይወት መለየት ወይም ዓለምን አለመምሰል
ለ. ፈቃዱን ማወቅ
ሐ. ፈቃዱን ማስተዋል ና መፈጸም

ሀ. የመጀመሪያውን ሃሳብ ከላይ በመጠኑም ቢሆን የተብራራ ይመስለኛል

ለ. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ የምንችለበት ዋነኛውና የመጀመሪያው መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና በማጥናት ሲሆን ይህንንም ያነበብነውን የእግዚአብሔር ቃል በእግዚአብሔር ጸጋና መንፈስ በመሆን በህይወታችን መፈጸም ነው፡፡

ለምሳሌ የእግዚአብሔር ቃል በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፥3 ላይ “የእግዚአብሔር ፈቃድ ከዝሙት ርቃችሁ እንድትቀደሱ ነው፡፡ ደግሞም እያንዳንዱ የገዛ ሰውነቱን በቅድስናና በክብር መያዝ እንዳለበት እንዲያውቅ ነው፡፡ ይህም እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አህዛብ በፍትወት ስጋ ምኞት አይሁን” ይላል፡፡

እንደዚሁም በ1ተሰሎንቄ 5፤16-18 “ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ሳታቋርጡ ጸልዩ በማንኛውም ሁኔታ አመስግኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእናንተ ይህ ነውና”፡፡

የሚለውን ቃል ስንመለከት የእግዚአብሔር ቃል ፈቃዱን በግልጽ ሁኔታ እንዳስቀመጠ እናያለን፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ፈቃዱን የምናውቅበት እግዚአብሔርንም ደስ የምናሰኝበት ህይወት የምንቀበልበት ቅዱስ መጽሐፍ ነው፡፡

ሐ. ፈቃዱን ማስተዋልና መፈጸም

- ነብዩ ሆሴዕ እንደተናገረው አስተዋይ የእግዚአብሔርን መንገድ ያስተውላሉ ይሄዱበታልም፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ማስተዋል እንደሚገባን የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል፡፡

ከላይ ባለው ሃሳብ እንደጠቀስኩት ብዙዎቻችን በመቅደሱ ላይ የተገለጠውን የእግዚአብሔር ቃል የምናውቅ ቢሆንም ያንን ያወቅነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም አስቸጋሪ ይሆንብናል፡፡ ስንቶቻችን የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያዘን ራሳችንን በቅድስናና በንጽህና ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር ቅዱስና ህያው መስዋዕት አርገን እናቀርብ ይሆን? ስንቶቻችን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ እያወቅን ሁልጊዜ ደስ ይለናል? ሳናቋርጥ እንጸልያለን? በሁሉ እናመሰግናለን? የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ለብዙዎቻችን የተሰጠን ቢሆንም መፈጸም ግን አዳጋች የሆነብን ለምን ይሆን? ምክንያቱ አንድ ነው እሱም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካወቅን በኋላ የእግዚአብሔር ቃል ፈጽሙት ሳይሆን አስተውሉት ይለናል፡፡

ማስተዋል ደግሞ መገለጥ፣ ማሰላሰልና ባወቅነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ መጸለይ ማለት ነው፡፡ ያለማስተዋል የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም ሞኝነት ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ ዮሴፍ ለፈርኦን ህልምን መፍታት ወይም ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን መፍትሄውም ከእግዚአብሔር ተሰጥቶት ነበር፡፡

በእግዚአብሔር ቃል የተገለጠውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ለመፈጸም የእግዚአብሔር ቃል ከማንበብ ወደ ማጥናት ከዚያም ወደ ማሰላሰል ከዚያም ወደ መገለጥ ልንደርስ ይገባናል፡፡ በተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ልንጸልይና ማስተዋልን ከእግዚአብሔር ልንቀበል እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ዘመኑን ስንመለከት እጅግ አስጨናቂና እግዚአብሔርን መስለውፈ መኖር ለሚወዱ አስቸጋሪ የሆነበት ጊዜ ላይ ደርሷል ነገር ግን ብዙዎቻችን ዘመኑን ማስተዋል ስላልቻልን ክርስትናችን ኢየሱስን መለያ መሆኑ ቀርቶ ዓለምን እያሳየን እንኖራለን፡፡ ከፍቅር ይልቅ መገፋፋትና ጥላቻ በህይወታችን ነግሷል፡፡ ከይቅርታ ይልቅ መራርነትና በቀልን መርጠናል፡፡

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚል በመጨረሻው ዘመን ሰዎች ወደ ክፋት እንደሚሮጡ እኛም ህይወታችን ከመልካም ነገር ይልቅ ክፉ ነገርን ማድረግ ይሻለዋል፡፡ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዕውነት ይልቅ ተድላን፣ መደሰትን፣ ያለ ጭንቅ መኖርን መርጠዋል ወገኖቼ ሆይ ሁላችሁ ኢየሱስ ይመጣል፡፡ አዎን ይመጣል፡፡ ስንቶቻችን እንሆን መቅረዛችን በዘይት ሞልቶ መብራታችንን አብርተን የምንጠብቀው? እግዚአብሔር ሁላችን ማስተዋልን ይስጠን እላለሁ፡፡

ከእግዚአብሔር አብ ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም፣ ፍቅርም ከእምነት ጋር ለሁላችን ይሁን፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማይጠፋ ፍቅር ለሚወዱ ሁሉ ጸጋ ይሁን፡፡

ወንድማችሁ! ጌርሳም አሸናፊ

# ከወንድም ስዩም ወርቅነህና ከባለቤቱ ከእህት ዘውዲቱ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ



ሮሆቦት- ጌታን እንደ ግል አዳኝ አድርገህ መቼ እንደተቀበልክ እና ሴፕቴምበር 9/07 በህይወትህ የተከናወነውን አስደናቂ ሁኔታ በዝርዝር ብትነግረን?

መልስ - ጌታን እንደ ግል አዳኜ አድርጊ የተቀበልኩት አሜሪካን አገር በመጣሁ በመጀመሪያው ዓመት ላይ ነበር ማለትም እ.አ.አ. በበ1996 ነበር። በሜትሮዶም ውስጥ የቢልግርሃም ሚኒስትሪ ባዘጋጀው ክሩሴድ ላይ ለመካፈል እኔና ባለቤቴ ሄደን ነበር በመሆኑም በዕለቱ ቢልግርሃም ወንጌልን ከሰበኩ በኋላ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችሁ አድርጋችሁ ለመቀበል የምትፈልጉ ወደ ፊት ውጡና ይጸለይላችሁ የሚል ጥሪ ባቀረቡት መሰረት እኔም ተነስቼ ወደፊት በመሄድ ጌታን እየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ተቀበልኩት። ከዚህ ቀን በፊት እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ህዝብ ምን ይላል በሚል ርዕስ በዶክተር ቶሎሳ ጉዲና የተጻፈ መጽሐፍ አንድ ወንድሜ ሰጥቶኝ አንብቤ ስለነበር ክርስቲያን ለመሆን ልቤ በጣም ተነሳስቶ ነበር። በተለይ የሃገርና የወገን ጉዳይ በጣም ይሰማኝ ስለነበር ለካ ክርስቲያንም ሆኖ በነዚህ ጉዳዮች ላይ ለውጥ ማምጣት ይቻላል የሚለው ነገር ወደ ውስጤ ስለገባ ለጥሪው አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት እየሱስን ወደ ህይወቴ አስገባሁት።

ከዚያም በኋላም ከቤተሰቤ ጋር በመሆን በሚኒሶታ ወደ ምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በመምጣት በየሳምንቱ እሁድ የሚሰበከውን ስብከት በሚገባ መከታተል ጀመርኩ። በነዚህ ጊዜያት በተለይ በፓስተር እንድርያስ ከሚቀርቡት ትምህርቶች የተነሳ ለዘመናት በውስጤ ጥያቄ ፈጥረውብኝ የነበሩትን ብዙ ነገሮች መልስን አገኙ። በተለይ ከሃይማኖት፣ ከባህልና ከልማዳዊ አመለካከቶች ቀስ በቀስ እየተላቀቅሁ መጣሁ። ከክርስቶስም ወንጌል ጋር መገናኘት ጀመርኩ ባጠቃላይ በነዚህ ጊዜያት ያገኙሁት ትምህርት ህይወቴን እያጠራና ወደ እግዚአብሔር እያስጠጋኝ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እግሬ እንዲተከል ረድቶኛል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሴፕተምበር 9/07 እግዚአብሔር አስደናቂ በሆነ መንገድ በመንፈሱ በታላቅ ሁኔታ ተገናኘኝ። ቀኑ ዶክተር ተስፋ ወርቅነህ በቤተክርስቲያናችን ተጋብዘው መጥተው ያገለገሉበት ቀን ነበር። የዕለቱ ትምህርታቸው ያተኮረው የክርስቲያን ህይወት ክርስቶስን መምሰል እንዳለበት ነበር በተለይ አንድ ክርስቲያን በህይወቱ የመንፈስ ፍሬዎች ሊታዩበት እንደሚገባ በጣም አበክረው ይናገሩ ነበር ለዚህም ምሳሌ ሲሰጡ ቢላ ቢላነቱ የሚታወቀው እስከቆረጠ ድረስ ብቻ እንደሆነ ሁሉ ክርስቲያንም የክርስቶስ ተከታይ መሆኑ የሚታወቀው የመንፈስ ፍሬዎች በህይወቱ ሲገለጹና ክርስቶስን እየመሰሉ ሲኖሩ ሲጓዙ እንደሆነ በዝርዝር ያስረዱ ነበር።

ይህንን ትምህርት በተመስጦ ነበር ልቤ ተነክቶ የተከታተልኩት ራሴንም በትምህርቱ ውስጥ አይ ነበር። በመጨረሻም ዶክተር ተስፋ ትምህርታቸውን እንዳበቁ የደህንነት ጥሪ አደረጉ በዚህ ጊዜ ምንም ልቋቋመው የማልችለው ሃይለኛ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጥም በውጪውም ሰውነቴ ላይ አረፈ። በልቤ ውስጥ እጄን በማንሳት ለጥሪው ምላሽ እንድሰጥ በሃይል ይሰማኝ ነበር። በሃሳቤ ደግሞ ከዚህ በፊት ጌታን ተቀብያለሁ ይህ የመጣብኝ ስሜት ከስጋዬ ቢሆንስ እያልኩ ከራሴ ጋር ሙግትና ትግል ጀመርኩ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ ከውስጥ የሚሰማኝ ስሜት አይሎ እጄን አወጣሁ እጄን ለማውረድ ስሞክር በሰውነቴ ላይ ህመም ይሰማኛል ከፍ ሳደርገው ያ ህመሙ ከኔ ይሄዳል በሁኔታው በመገረምና በመንቀጥቀጥ ጸሎት ተጸልዮ እንዳበቃ ከጎኔ ተቀምጣ ለነበረችው ባለቤቴ ሁኔታውን ከነገርኳት በኋላ ፓስተር እንድርያስ እንዲጸልይልኝ ወደ እርሱ በመሄድ የሆነውን ነገር ሁሉ እያለቀስኩ ነገርኩት። እርሱም ልክ አንድ አዲስ ሰው ወደ ጌታ ሲመጣ እንደሚጸለይለት አይነት ጸሎት ጸለየልኝ እሱም ከጸለየልኝ በኋላ በውስጤ ከእንግዲህ ወዲህ ብሞትም ግድ የለኝም አልኩ ከአሁን በኋላም ህይወቴ ክርስቶስን እየመሰለ ፍሬ እያፈራሁ ለመኖር ወሰንኩ ለእግዚአብሔርም በምትፈልገኝ ቦታ ሁሉ እየተገኘሁ አገለግልሃለሁ ብዬ ቃል ገባሁለት።

ሮሆቦት - ከዚያች ቀን ውሳኔ በኋላ በህይወትህና በኑሮህ እየተካሄደ ያለ ምን አዲስ ነገር አለ?

መልስ - ከዚያች ቀን በኋላ በጣም የሚያስደንቁ ነገሮች በህይወቴ ሲከናወኑ አይቻለሁ እየተከናወኑም ናቸው ከነዚህም መካከል በዚያው ዕለት ያጋጠመኝ ሁኔታን ብናገር በዕለቱ የቤተክርስቲያኒቱ ፕሮግራም ተጠናቆ እንዳበቃ እኔና ቤተሰቤ ወደ አንድ ስፍራ በቀጥታ ሄደን ነበር በዚያ ስፍራ ከረዥም ጊዜ በፊት በአንድ ጉዳይ ተቀያይመን ሳላናግረው የቆየሁትን ጓደኛዬን ፊት ለፊት አየሁት በዚህ ጊዜ በቀጥታ ወደ እርሱ በማምራት እጆቼን ዘርግቼ በማቀፍ ወንድሜ በድያሃለሁና ይቅር በለኝ እልኩት እርሱም በሁኔታው በመገረምና በመደናገጥ እኔ ነኝ እንጂ አንተ አልበደልከኝም ይልቅ ይቅር በለኝ በማለት ምላሽ ሰጠኝ ይህ ሁሉ ሲሆን አቅፌው አልቅስ ነበር ከዚያም ከልብ በሆነ ይቅርታ ይቅር ተባብለን ሰላምን መሰረትን ይህ በውስጤ የፈሰሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ወንድሜን ይቅር እንድልና እኔም ይቅርታ እንድጠይቅ እንደረዳኝ ሳይ በህይወቴ ትልቅ ለውጥ እንደተካሄደ እንዳስተውል አደረገኝ።

ሌላው በጣም የሚደንቀኝ ነገር ደግሞ ከዚያች ቀን በፊት ማለትም ከተወሰኑ ቀናቶች ጀምሮ ትልቅ የመንፈስ ውጊያ በውስጤ ይካሄድ ነበር ይኸው የሞት ድምጽ በሃሳቤ እየመጣ ያስፈራራኝና ያስጨንቀኝ ነበር ከእኔም እንዲወገድ እጸልይና እገስጽ ነበር ሆኖም በሃሳቤ ተመላልሶ መምጣቱ አልቆመም ነበር ነገር ግን በዚያች ቀን አስደናቂ በሆነችው የእግዚአብሔር ጣት ከተነካሁ በኋላ ያ የሚያስፈራራኝና የሚያስጨንቀኝ የነበረው ነገር ሁሉ እንዴት እንደሆነ በማላውቀው ሁኔታ ከእኔ ተወግዶ አገኘሁት እኔም ነጻ ወጣሁ የእግዚአብሔር ስም ብሩክ ይሁን። እግዚአብሔር በመንፈሱ በልዩ ሁኔታ ከተገናኘኝ ከዚያች ቀን በኋላ በህይወቴ ያየሁት ሌላው ለውጥ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል በማነብበት ጊዜ እግዚአብሔር ቃሉን ይገልጽልኝና ያበራልኝ ጀመር በመሆኑም ልክ እንደዚያች ሳምራዊት ሴት ጌታ እየሱስ የውስጧን ከነገራት በኋላ ወደ ከተማ ተመልሳ ላገኘችው ሰው ሁሉ ስለ እየሱስ እንደተረከችና ኑ ላሳያችሁ እንዳለች ሁሉ እኔም የበራልኝን እውነት ለምቀርባቸው ሰዎች ለመንገር ሃይል አገኘሁ። በተለይ በባህል፣ በታሪክ፣ በሃይማኖትና በልማድ ሽፋን ለሚመላለሱ ሁሉ እግዚአብሔር በእውነትና በመንፈስ የሚመለክ አምላክ መሆኑን በመሆኑም ይህንን አምላክ ማወቁ አስፈላጊእንደሆነ ባገኙሁት አጋጣሚ ሁሉ መናገር ጀመርኩ።

ሮሆቦት - በቤተክርስቲያን ውስጥ እየተመላለሱ ለውጥ በህይወታቸው ሊያዩ ላልቻሉ ወይም ጌታን እንደግል አዳኛቸው አድርገው ላልተቀበሉ ሰዎች ምን የምትለው ነገር አለ?

መልስ - በመጀመሪያ በተለይ ለሃገር ለወገን ትልቅ ሸክም ላላቸው ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ቢቀበሉ ያ ሁሉ የሚቀርባቸው ለሚመስላቸው ሰዎች እኔም በዚያ ውስጥ ስላለፍኩ የምለው ነገር አለ ይኸውም ሸክሙ ካለ ክርስቲያንም ሆኖ እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ እያመለኩ ለሃገርና ለህዝብ የሚጠቅምን ነገር በማድረግ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል በተለይም ደግሞ እውነት ክርስቶስ ስለሆነ በእርሱ ውስጥ ሆኖ በእውነት ላይ በመቆም ህዝብን ማገልገል እንደሚቻል ለማሳሰብ እወዳለሁ። ከዚህም በተጨማሪ ታሪክ የሚሰራ እንጂ የሚወራ ብቻ ስላልሆነ በፖለቲካ በባህል፣ በሃይማኖትና በልምድ ሽፋን ታሪክን እያወራን ብቻ ከምንኖር ይልቅ በህይወታችን ታሪክን ሰርተን ለውጥን አምጥተን ለመጪው ትውልድ የሚተላለፍን ነገር አድርገን እንለፍ እላለሁ። ለዚሁ ሁሉ እየሱስን እንደግል አዳኝ አድርጎ በመቀበል በእግዚአብሔር ቃል እውቀት መመላለስ የሚጠቅም መሆኑን ጨምሬ ለመናገር እወዳለሁ። በተለይ በክርስቶስ ውስጥ የሚገኘው ህይወት ሰው ካልቀመሰው የማያውቀውና የማይረዳው ደስታና ሰላም ያለበት ህይወት ስለሆነ ጌታን እንደግል አዳኝ በመቀበል ይህንን ደስታና ሰላም በህይወታቸው እንዲለማመዱ ለማደፋፈር እወዳለሁ።

በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ለረዥም ጊዜ ኖረው በህይወታቸው የሚፈልጉትን ያህል ለውጥ ለማየት ላልቻሉ ሰዎችም የምለው አለ ክርስትና ሃይማኖት ሳይሆን ህይወት ነው። ስለዚህ በሃይማኖት ሽፋን ፍሬን ሳያፈሩ ከመመላለስ ይልቅ በክርስቶስ ነጻ እንደወጣ ህዝብ በቃሉ በመኖር የመንፈስን ፍሬ እያፈሩ እንዲኖሩ እመክራለሁ። በተለያየ ምክንያት ሸክማቸው ለከበደባቸው ሰዎችም ዛሬም እየሱስ "እናንተ ሸክማችሁ የከበደባችሁ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ይላቸዋል ስለዚህ በቤቱ እየተመላለሱ በስጋትና በጭንቀት ያሉ ቢኖሩ ሸክማቸውን በእግሩ ስር በማራገፍ ቀላል የሆነውን የክርስቶስን ቀንበር ተሸክመው በህይወት እንዲኖሩ እመክራለሁ።

ሮሆቦት - ባለቤትህ ከአንተ ቀደም ብላ ጌታን እንደተቀበለች እናውቃለን ከህይወቷ ምን የተማርከውና ያየኸው የተለየ ነገር አለ?

መልስ - በዚህ አጋጣሚ አንድ ሳልናገር የማላልፈው ትልቅ ነገር አለ፣ ፣ ይኸውም ባለቤቴ ከእግዚአብሔር የተቀበልኳት አስደናቂ ስጦታዬ መሆኗን ነው ህይወቷ ዕለት ዕለት ክርስቶስን ያሳየኝ ነበር እግዚአብሔር መልካም ሚስትን ብቻ ሳይሆን በኑሮዋ የክርስቶስን ህይወት የምታሳይ ለእግዚአብሔርና ለባሏ ፍቅርና አክብሮት ያላትን ሚስት ነው የሰጠኝ ዛሬ ልጆችንን እንደምታስተምረው ሁሉ ጌታን ባላወኩባቸው ጊዜያት እኔንም የእግዚአብሔርን ቃል ታስተምረኝና ትጸልይልኝ ስለነበር ህይወቷ ይማርከኝ ነበር። አሁን ዞር ብዬ ሳየው እግዚአብሔር ከኔ ጋር ሆኖ በምን ዓይነት ሁኔታ አሳልፎ እዚህ እንዳደረሰኝ ስመለከት የሆነልኝ ነገር በህይወቴ የሆነው በአጋጣሚ ሆነ እድለኛ በመሆኔ ሳይሆን እግዚአብሔር ስለረዳኝ፣ ስለወደደኝና ስለተጠነቀቀልኝ እንደሆነ ለመረዳት ችያለሁ እግዚአብሔር በትዳራችን በብዙ በረከት እየባረከ እዚህ አድርሶናል ስሙ ለዘለዓለም የተመሰገነ ይሁን።

ከወንድም ስዩም ጋር ያደረግነውን ቃለ መጠይቅ እንዳጠናቀቅን ለባለቤቱ እህት ዘውዲቱ ሁለት ጥያቄዎችን ጠይቀናት ነበር በመሆኑም ባለቤትሽ ጌታን ከመቀበሉ በፊት እምነትሽን በተመለከተ ችግር ፈጥሮብሽ ያውቃል? ብለን ለጠየቅናት ጥያቄ ምላሽ ስትሰጥ ባለቤቴ ለእግዚአብሔር ለሰውም የተመቸ ልክ እንደ ህጻን ልጅ ልብ ተንኮል የሌለበት መልካም ልብ ስላለው አንድም ቀን እምነቴን ተቃውሞ አያውቅም ነበር እግዚአብሔር እሱን ስለሰጠኝ በጣም አመሰግነዋለሁ።
እግዚአብሔርን መፍራቱና ማክበሩ እኔን ከሚያስደስተኝ ነገር አንዱና ትልቁ ሲሆን የእኔን የክርስትና ኑሮ አቃልሎኛል እንደውም ወደ ቤተክርስቲያን አብረን በመሄድ በቤታችንም አብረን በመጸለይ ቃሉን በ መካፈል ይተባበረኛል እንጂ በፍጹም ተቃውሞ አልነበረውም በእኔ በኩል ወደና ፈቅዶ ጌታን እስኪቀበል ድረስ አንድም ቀን ወደ እውነቱ ከመውሰድ በስተቀር ተጽእኖ አድርጌበት አላውቅም ነበር ሆኖም ለእግዚአብሔር አደራ ሰጥቼው ስለነበር እግዚአብሔር በቀጠረው ሰዓት አንድ ቀን በገዛ ፈቃዱ ጌታን እንደ ግል አዳኙ ተቀበለ ከዚያ በኋላ በመንፈሳዊ ነገር እንዲያድግ እንዲረዱት ዓይኔን በአንዳንድ ሰዎች ላይ አድርጌ ነበር ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በራሱ ሰዓት ተገናኝቶት ይኸው ዛሬ ለመመስከር አብቅቶት ሳይ ለኔ ከዚህ የሚበልጥ ደስታ የለኝም የእግዚአብሔር ስም ለዘላለም የተባረከ ይሁን። በመንፈስ ቅዱስ ከተነካበት ጀምሮ በህይወቱ ትልቅ ለውጥ ስላየሁ እኔም ምስክር ነኝ እላለሁ።

ሮሆቦት - ባሎቻቸው ጌታን ለማያውቁ ወይም ሚስቶቻቸው ጌታን ለማያውቁ ሰዎች እግዚአብሔር ካደረገልሽ ምህረትና ቸርነት በመነሳት ምን የምትመክሪያቸው ነገር አለ?

መልስ - በመጀመሪያ ደረጃ የትዳር ጓደኞችንን እንደለ (ች) መቀበሉ በጣም መልካም ነው። አካሄዳቸውንና አነጋገራቸውን እየተከታተልን እናርማለን ብለን ከምናስመርራቸው ይልቅ ወደ እግዚአብሔር ፊት ነገሩን በማቅረብ እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር ፊት እንደቃሉ በሚገባ በመመላለስ ጌታ እንዲነካቸው ሳናቋርጥ ብንጸልይላቸው የተሻለና የተገባ ነው እላለሁ። በአጠቃላይ እናድናቸዋለን ብለን በድርጊታችን እንዳናጠፋቸው አጥብቀን ልንጠነቀቅ ይገባል። በተለይ ቀደም ሲል እንዳልኩት ትክክል ያልሆነ ነገር ሲሰሩ በምናይበት ጊዜ በመቃወም መልክ ሳይሆን በእውነትና በፍቅር ልናርማቸው ይገባል፣ ፣ በመጨረሻም አጥብቄ ልናገር የምወደው በህይወታችን ክርስቶስን እንዲያዩ አካሄዳችንን እየተጠነቀቅን በመራመድ ጌታን እንደ ግል አዳኝ አድርገው እንዲቀበሉ ልባቸውን ልናነሳሳ ይገባል እላለሁ። እኔን የረዳኝ እግዚአብሔር በዚህ ሁኔታ ያሉትን ሁሉ ይርዳቸው እላለሁ ስሙ ይባረክ።

ከወንድም ስዩምና ከእህት ዘውዲቱ ጋር የተደረገው ቃለ ምልልስ እንዳጠናቀቅን ወንድም ስዩም የሚከተለውን ግጥም ጽፎ ሰጥቶናል እኛም ለአንባቢያን እንደሚከተለው አቅርበናል።

## ያ ቢለኝ ይኽ ቢለኝ

ያ ቢለኝ ይኽ ቢለኝ
እኔ አልሰማም ጆሮም የለኝ
አይቸዋለሁና ማን እኔን እንዳወጣኝ
አውቄዋለሁና ማን እኔን እንዳዳነኝ
በታሪክ ስም በባህል ስም የፊጥኝ ያሰረኝን
በቃህ አልኩት ለዘመናት አደንዝዞ የገዛኝን
ወግ ልማዴን ዘር ማንዝሬን አልፈለገኝ
ብቻ ከኔ የፈለገው ቅንነቴን ንጹህ ልቤን
መች ሆኖ የያዘኝ እኔነቴን የትምክህት ማንነቴን
እሮይ አልኩኝ በረዥሙ ተነፈስኩኝ
የያዘኝን አበሳዬን ተገላገልኩ ነጻ ሆንኩኝ
ያ ቢለኝ ይኽ ቢለኝ
እኔ አልሰማ ጆሮም የለኝ
አይቸዋለሁና ማን እኔን እንደታደገኝ
አይቸዋለሁና ማን እኔን እንዳዳነኝ
ስሙ ይክበር ለዘላለም ህይወት ሆኖ ለበዛልኝ
ጨለማውን ገፎ ብሩህ ተስፋ ላወጣልኝ
ለእግዚአብሔር ልጅ ለእየሱስ ተማረኩኝ
ህይቴን በሞት ሞቴን በህይወት ለሱ ለወጥኩኝ
ከእንግዲህ ፣
ያ ቢለኝ ይኽ ቢለኝ
ታሪክ ቢጠቀስ ወግ ልማዱን ቢጠርቀኝ
እኔ አልሰማም ጆሮም የለኝ
ከዚያ የሚበልጥ መንገድ ህይወት አለኝ
እየሱስ ህይወት ነው!!!!

# ከጠላት እስራት ነጻ ወጣሁ



በምስክርነቱ ቃል ድል ነሱ ስለሚል ቃሉ እኔም ሰይጣንን ጠላትን በጌታ በእየሱስ ክርስቶስ ድል ነስቻለሁ፡፡ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ዚህ ምድር ላከ ልጁም ለኔ ሲል በመስቀል ላይ ሞቶ ህይወትን ሰጥቶኝ በፊት ያልነበረኝን ሰላምና ደስታ ሞልቶ ዛሬ ታሪኬን እንድመስክር ለረዳኝ እግዚአብሔር ምስጋናና ክብር ከዛላለም እስከ ዘላለም ይሁን እላለሁ፡፡

ይህን ለማለት የቻልኩበት እና ለማለት ያስቻለኝ የእግዚአብሔር ቃል በኔ ስለሰራ ነው፡፡ እኔ ከህጻንነቴ ጀምሮ በሽተኛ የነበርኩ ነኝ እንደ ሰው ቆሜ እንደ ልጅ ተጫውቼ እንኳን አላወኩም ሁልጊዜ ስለምታመም የኔ ጓደኛ አልጋዬ ነበር በቤተሰቤ እና በሚያውቁኝ ሁሉ መለያ ስሜ በሽተኛው ልጅ በመባል ነበር፡፡

ይህ ነው የማይባል በሽታ በእኔ ላይ ነበር አንድ ሰው ምግብ ቤት ሄዶ ምግብ ሲቀርብለት የምግብ ዝርዝር ይቀርብለታል እኔ ደግሞ ወደ ሆስፒታል ስሄድ የበሽታዬን ዝርዝር ነበር ጽፌ የምቀርበው ታዲያ ምንም መፍትሄ አላገኝም፡፡ እንዲህ እያለሁ ሰርጌ ደርሶ የሰርግ ካርድ ለሰዎች ሲታደል ሰዎች የእግዚአብሔር ስራ ድንቅ ነው ያቺ ልጅ አድጋ ለትዳር በቃች ነበር የሚሉት ለኔ ግን የአንድ ቀን ደስታ ነበር በሁለተኛው ቀን አልጋዬ ላይ ተኝቼ ነበር ጆሮዬ በደንብ አይሰማም፤ ምግብ አልበላም፤ ምንም ዓይነት ምግብ አይስማማኝም፡፡ እናቴ የሰርጌ ቀን እንደማንኛውም ልጅ አግብቶ እንደሚሄድ ሰው ማልቀስ አለ እሷ ግን ልጄ ከዚህ ወጥታ ምን ልትበላ ነው ውሃ የማትጠጣ ልጅ ብላ ብዙ አምርራ ስታለቅስ ነበር ሰው የጠየቃት በመሄዴ ሳይሆን በበሽታዬ ነበር ሌሊት ተኝቼ በሬ ላይ ቆማ ታዳምጣለች ጧት ነግቶ በሬ ላይ አገኛትና ምግብ ይዛ ትጠብቀኛለች በጧት ሆዴ ምግብ ካልበላሁበት ሆዴን ይቆርጠኝ ነበር ሌሊት ይርበኛል ግን የምትሰጠኝን አልበላውም እንቅልፍ አልተኛም ያ ሁሉ ሲሆን እናቴ አይዞሽ እግዚአብሔር ቸር ነው ይምርሻል ትለኛለች፡፡

ከወለድኩኝ በኋላ ግን ለትንሽ ጊዜ ጤና ከሆንኩ በኋላ ከፍተኛ አስም ደርሶብኝ ለስምንት ዓመት አብሮኝ ኖረ በመቀጠል ጨጓራዬ በመላጥ ወደ አልሰር ተለውጦ ከፍተኛ መድሃኒት እውጥ ነበር እሱን እየወጥኩኝ ምግብ አልበላም ወተት እራሱ አይረጋልኝም በመጨረሻም ዶክተሩ ጨጓራዋ ተልጦ ወደ ካንሰር ከመለወጡ በፊት ከሚያቃጥል ምግብ ትታገድ ተብሎ ለ6 ወር እንጀራና በርበሬ አልበላም ይህ በእንዲህ እያለ ጆሮዬን ለመታከም እስራኤል አገር ከእናቴና ከአባቴ ጋር ሄድኩኝ እዛ ህመሜ በርትቶብኝ ጆሮዬን ትንሽ ሲሻለኝ ሌላው ያሰቃየኝ ነበር እራሴን ልቤን በጣም ያመኝ ነበርና ሃኪሞቹ ቤተሰቤን እናንተ ወደ አገራችሁ ተመለሱ እሷ ትቆይ ብለው እኔ ለአምስት ዓመት እየሩሳሌም ቆየሁ ማንም ያውቀዋል እየሩሳሌም የክርስቲያን አገር ነው እኔም እናቴን አሁን እዚህ አገር ከቆየሁ ከበሽታዬ እድናለሁ አይዞሽ ስላት እሷ ደግሞ ዘመድ ወዳጅ በሌለበት እኔን ጥላ መሄዷ ከብዷት ወደ እግዚአብሔር ጸልያ አንተ ልጄን ጠብቅልኝ ብላ ትተውኝ ሄዱ፡፡

እኔም ከባዳ ጋር መኖር ጀመርኩኝ የነበርኩባቸው ኢትዮጵያውያን ነበሩ እቤታቸው ያው እንደ ኢትዮጵያ ምግብ ይዘጋጃል ሁሉም አለ ግን እኔ አልበላም ሌሊት ስተኛ እባንናለሁ ጆሮዬ ላይ ጭንቅላቴ ላይ ይጮህብኛል ምግብ እምቢ ስል እነሱ ይከፋቸዋል እኛን ከጠላሽን ሌላ ቤት ተከራይና ውጭ አሉኝ በበሽታዬ እግዚአብሔር ብቻ አልጠላኝም ሌሊት ስባንን ይቺ ልጅ እብድ ትሆን እያሉ ሁሌ ይፈሩኛል እኔ ግን በጣም ነበር ሰላም ያጣሁት እንደዚያ እያለ ሰዎች ሳውቅ ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄዱ ጓደኞች አገኘሁ ወደ ጎልጎታ ቤተክርስቲያን አብሪያቸው የሚሄዱ ልጆች ሲያዩኝ አንቺ ልጅ ከቤተሰብሽ ሌላ ሰው ቤት ምግብ አትወጂም እኛም ሰው ነን አትፍሪ ይሉኛል ችግሬን ግን እራሴ ነኝ የማውቀው፡፡

አንድ ቀን በጣም ታምሜ አንዲትን ልጅ ነግሬያት በታክሲ ወደ መጥምቁ ዮሃንስ የተወለደበት ቦታ የሃንስ ጸበል የሚባል ሄድን እዛ ውስጥ ተጠምቄ ጸበሉን ይገኤ መጣሁ ጸበሉም አመመኝ ምክንያቱም ውሃ አልጠጣም እንደ ውሃ ተቆጥሮ ነው መሰለኝ አመመኝ ከዚያ አቆምኩት ትንሽ ራሴን ተወኝ ይህ በእንዲህ እያለሁ በጣም ታመምኩና ወደ ሃኪም ሄድኩኝ እዛ ስሄድ ተስፋ የቆረጠ ነገር ዶክተሩ ነግሮኝ ወደ ቤቴ ተመለስኩኝ ተስፋ እግዚአብሔር እንጂ ሰው እንዳልሆነ አሁን ተረዳሁት ያም የሆነው በ2003 ነበር፡፡

እንዲህ ነበር በ2003 ዶክተሩ በቃ አንቺ እኖራለሁ ብለሽ ጤነኛ ነኝ ብለሽ ታስቢ ነበር ግን በበሽታሽ ላይ ያገኘሁት ውጤት በጣም አሳዛኝና አስፈሪ ስለሆነ እባክሽን ልጅና ቤተሰብ አለኝ ብለሻል እና በግምት ያንቺ ዕድሜ ዘመን ቢበዛ ሶስት ሳምንት ወይም ከዛ በታች ሊሆን ይችላል አለኝ ዕድሜ የሚጨምርና የሚወስን አንድ እግዚአብሔር እንደሆነ ቢያውቅ ምን ይደንቀው ነበር እና እንደዛ ሲለኝ እቤቴ እንዴት እንደደረሱኩ አላውቅም ለታክሲውን ሹፌር ያለኝን ብር ሁሉ ነው የሰጠሁት በመገረም ስወርድ ዝም ብሎ ያየኛል ምነው አሳነስኩ ስለው አይ ደህና ነሽ ነው ያለኝ እኔ እቤቴ ገብቼ ለእግዚአብሔር እንዴት ይሆን እምሆነው ብዬ ወደ እሱ ጸልዬ ስነሳ ቦርሳዬን ሳየው ባዶ ነው ለካ ተስፋ ስለቆረጥኩኝ ምን እንዳረኩ ተረዳሁ ያ ለበረከት ሆኖ ለሱ የሰጠሁት ብር የረሳሁት የሰራሁበት ቦታ ለምን አልወሰድሽም ተብዬ በማግስቱ የሁለት ወር ደመዎዜ ተሰጠኝ እንደዚህ እየታመምኩ ስራ በጣም እወድ ነበር ሁለት ስራ ሶስት ስራ እሰራ ነበር፡፡ እንዲህ እያለ በቃ እናቴ ቁርጥሽን እወቂ እዛው ሞቼ በልጄ ፊት ልቀበር ነው ብዬ አስብ ነበር፡፡

ወዲያው ትኬት ለመቁረጥ ስደውል ከዚህ ሳምንት እስከ ሚቀጥለው ሳምንት ሙሉ ነው አሉኝ ምን እንደማደረግ ጨነቀኝ ዶክተሩ ያለኝ ሶስት ሳምንት ትኬቱ ከዚያ በላይ ሰው አገር ልሞት እናቴን ቤተሰቦቼን እህቶቼን አሰብኩ ሙሉ ሌሊት ሳለቅስ አደርኩኝ ምግብ አልበላ ጓደኞቼ አገርሽ ለመግባት ምነው ተጨነቅሽ እንዳንቺ ሞልቶልን በሄድን ይሉኛል እግዚአብሔር የባረካቸው ሰዎች ሁሉ ከጎኔ አልተለዩኝም ጌታ የሰጠኝ ዘመዶች ናቸው፡፡

በኋላ ወደ ሃገሬ እንደምሄድ እዚህ ላሉት እህቶቸ ደውዬ ነገርኳቸው ወንድሜም ደስ አለው እዛ ሁልጊዜ የሚሰሙት ስለጦርነት ስለአደጋ ነበር እኔ እራሴ እግዚአብሔር ጥበቃው ስለአበዛልኝ ከአንዴም ሁለቴ ከቦንብ ተርፌያለሁ አንድ ቀን ስራ ረፈደብኝ አውቶብሷ አመለጠችኝ ብዬ ተደናግጬ ስወጣ ጧት የምይዛት ባስ ያመለጠችኝ እኔ ከምይዝባት ሁለት የአውቶብስ መቆሚያ በኋላ አረቦች አውቶብሷን በቦንብ አፈነዱት ሾፌሩም ተሳፋሪዎችም አብረው አለቁ ጓደኞቼ እግዚአብሔር ይወድሻል፡፡

አንቺ የምትይዥው ባስ ነበር ላንቺ ነበር ያሰብነው አሉኝ አይዞአችሁ እግዚአብሔር ከኔ ጋር ነው ብዬ ነበር ባልኩ በሶስተኛው ቀን ስራዬን ሰርቼ ስመጣ ከሌላው ቀን ቀደም ብዬ ወጣሁ ጎለጎታ ሁሌ አርብ አርብ ሄደን እንጸልያለን ሻማ እናበራለን ጌታ እየሱስ የነበረበትና የተቀበረበት ቦታ ነበርና እዛ ለመሄድ ቸኩዬ ቶሎ ወጥቼ እንደሄድኩኝ በሰዓቴ የምይዛትን ሳይሆን ቀደም ያለችውን ባስ ይዤ እንደሄድኩ ከምሰራበት ቦታ ስልክ ተደውሎ አንቺ የት ነሽ አሉኝ ጓደኞቼን ቸኩዬ ነው ለአለቃዬ አትንገሩብኝ አልኩኝ እንኳን ወጣሽ በአንቺ ሰዓት ከአንቺ ጋር የሚወጡ የነበሩ አውቶቢሷ ፈንድታ ከሰራተኞች ሶስት ሰዎች ሞቶ አሉኝ አእግዚአብሔር ይወድሻል አሉኝ ወይ አምላኬ ለካ አልተውከኝም ብዬ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀርብኩኝ በጎልጎታ ሆኜ በሳምንቱ ደግሞ የምከራየው ቤት የሚገርማችሁ በጣም እንቅልፍ ስለማልተኛ ብተኛም ሁለትና ሶስት ሰዓት ስለሆነ ከቤቱ እየመሰለኝ ቤት እቀያይራለሁ እንዲህ እያለሁ እቤት ልከራይ ጨርሼ ተነጋግሬ በማግስቱ ልፈራረም በቀጠሮ ላይ እያለሁ ከቀጠሮዬ አንድ ሰዓት በፊት ቤቱ በቦንብ አጠገቡ ካለው ትልቅ የገበያ ቦታ ጋር አብሮ ተቃጠለ ይገርማችኋል የዚያን ቀን መንገድ እየሄድኩ ነበር ስልክ የደወለችልኝ አንዷ ጓደኛዬ ይህ ቤት መቀየር ለአንቺ እንቅልፍ መፍትሄ አይሆንም ስለት ተሳይ ነበር የምትለኝ፡፡

ይኸው ፈነዳልሽ አለችኝ በቃ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው አሁንም ብዬ አለፍኩኝ ከዚህ በኋላ ነበር እግዚአብሔር እንድወጣና ሓገሬ እንድገባ መፍትሄ ሆኖ ጥበቃው በኔ ላይ ስለነበር ሓኪሙ እንደ ነገረኝ በቃ የኔ ነገር አበቃ ብዬ ስደመድም አለበቃም ገና ተዓምር ታያለሽ ብሎኝ ሓኪሙ ካለኝ አንድ ሳምንት አልፎ ወደ ሓገሬ ገባሁ ምን ልበላችሁ ቤተሰቤ ልጄ ሁሉም ዘመድ አዝማድ አንቺ ጉደኛ ልጅ እየሩሳሌም ሄደሽ መጣሽ እግዚአብሔር መቸም ተዓምረኛ ነው እድሜ ቀጥሎልሽ አምስት ዓመት ቆይተሽ መጣሽ በማለት ተደሰቱ እንደ ሰርግ ያህል የተሰማት እናቴ ነበረች ተመልሼ ወደሷ በጤና በመመለሴ እኔ ግን ውስጤ ሃዘን ነበር በሓሳቤ ያለው ደክተሩ ያለኝ ነበር፡፡ እናትዬ አይዞሽ አሁንም እድሜዬን ሙሉ ከአንቺ ጋር ነው የምኖረው ስላት እኮ አሁንስ የትም አትሄጅም ድነሽ መጥተሻል ስትለኝ እኔ እንባ አንቆኝ አለቅሳለሁ ምክንያቱም የሚታየኝ አጭር እድሜ ብቻ እንደሆነ ስለአወኩት፡፡ ምነው ሰው ሁሉ እግዚአብሔርን እያሰበ እሱ ባለው ብቻ መኖር እንደምንችል ብናውቅ ባልተጨነቅን ነበር የእግዚአብሔር ቃል አትጨነቁ ይላል መጨነቅ እግዚአብሔርን አለማመመን እንደሆነ ማወቅ ይገባናል፡፡

ኢትዮጵያ እንደ ገባሁ በሳምንቴ እስከ አሁን እንግዲህ እድሜዬ ከቆየ እስኪ ሽንኮሩ ጠበል ልሄድ ብዬ ለማንም ሳልናገር ሽንኮራ ጠበል ሄጄ በዚያ በገደል ስንከራተት ቆይቼ አሰብኩ በአምስተኛው ቀን ሌሊት ተኝቼ የሆነ ሰው በቃሽ ሂጂ ተነሽ ይለኛል እዛ መብራት የሌለበት አገር ነው ደንግጬ ባንኜ በጣም ፈራሁና ተነሳሁ ወዲያውኑ ተነስቼ ወደ አዲስ አበባ ሄድኩኝና በቃ ድኜ ይሆናል ብዬ ወደ ሃኪም ቼክ ላደርግ ብዬ አንደኛውን እህቴን ውሰጂኝ ብዬ ሄድኩኝ እሷን ውጪ ብሎ ለእኔ በቃ በጤናሽ ላይ ምንም ጥሩ ነገር አላየሁብሽም እና እራስሽን እያዝናናሽ ከቤተሰብሽ ጋር ቆይ ብሎ ማስታገሻ ሰጥቶኝ ሸኘኝ እህቴ ለምን አስወጣኝ ብላ ደነገጠች እኔ ግን አይዞሽ እግዚአብሔር ከኔ ጋር ነው ምንም አልሆንም ከፍተኛና አስጊ ቢሆን ማስታገሻ ሰጥቶኝ ሂጂ አይለኝም ብዬ አጽናንቻት ተስፋ ቆርጬ ወደ ቤቴ ተመለስኩኝ በሳምንቱ ተዓምሩ የማያልቅበት አምላክ ወደ አሜሪካ እንደሚሄድ ተነገረኝ እኔም ለቤተሰቤ አልሄድም ሁለተኛ ስደት አላይም አልኳቸው እንደዚህ ያልኩት በውስጤ ምን እንዳለ ስለማውቅ ነው እንደዛ ሆኖ ወዲያው በወሩ ቪዛው አልቆ ከቤተሰቤ ጋር መጣን አሁንም እንደገና ታምሜ ምግብ አልበላ አልጠጣ የምበላው አይረጋልኝም እናትና ኣባቴም ለእህቶቼና ለወንድሜ ለእናንተና ለእግዚአብሔር ሰጥተናት እንሄዳለን ብለው ጥለውኝ ሄዱ፡፡

እኔም በጣም ታመምኩኝ ሁለቱን እህቶቼን ጠርቼ ሆስፒታል ሄድኩኝ ሰርጀሪ በአስቸኳይ ትደረግ ብለው ለእስፔሻል ዶክተር ተላኩኝ እህቶቼ በጣም ተጨነቁ እህቴም ወደ እግዚአብሔር ጸሎት ማቅረብ እና መለመን ነው ብላ ቀንም ማታም ይጸልዩ ነበር እስኪ የእናንተ ጌታ ካደነኝ እያልሁ ውጡ ብዬ ከሆስፒታል አስወጣኋቸው፡፡ ሰይጣን በምድር የመኖርያሽ ጊዜ አለቀ ይለኛል እኔ ደግሞ የእግዚአብሔር ነኝ የአንተ አይደለሁም እለዋለሁ ይህ በእንዲህ እንዳለ በማግስቱ ሰርጀሪ እንድደረግ ተቀጥሬ ወደ ሌላ ዶክተር ተጽፎልኝ ሄጄ ዶክተሯ እኔ የራሴን ምርመራ ካደረኩኝ በኋላ ነው ሰርጀሪ የምትሆነው አለችኝ እህቶቼ ኧረ አትቆይም በአስቸኳይ ትደረግ ነው ያሉት ሲሉ ምንም አይደለም አትጨነቁ ስትል እህቴ በቃ እግዚአብሔር ሊያደረግ ያለው ነገር አለ አይዞሽ ብላ ለትንሿ እህቴ ታስረዳት ነበር እኔ ግን አልነግራቸውም ብዬ እንጂ እንዳበቃልኝ ውስጤን ይነግረኛል፡፡

ከዚያ ከሁለት ሰዓት በኋላ የምርመራው ውጤት መጣ እህቶቼ ያለቅሱ ነበር ግን ወዲያው ዶክተሯን ሲያዩአት ተጽናኑ በዶክተሯ በኩል እግዚአብሔር የሚያጽናና መንፈስ የላከ ይመስል ነበር ዶክተሯም አይዞአችሁ ደህና ናት ምንም ለሰርጀሪ የሚያበቃ ነገር አላየሁም እና በሰላም ወደ ቤቷ ዛሬውኑ ትሄድ አለችኝ ወይ አምላክ ሆይ የልጆችህን ጭንቀት ታያለህ ለካ ብዬ ታዲያ ለምን ሰላም አጣለሁ ብዬ ወደ ቤታችን ስንገባ እህቶቼ ጸሃዬ መጽሓፍ ቅዱስሽን አንብቢ የእግዚአብሔር ቃል ያድንሻል አሉኝ እሺ ብዬ መጽሓፍ ቅዱሴን አልጋዬ ላይ ቁጭ ብዬ ማንበብ ስጀምር እቤቱ ጭልም ይልብኝና ድካም ይሰማኝና እጄ መጽሐፍ ቅዱስ የያዘበት ሲቃጠል እራሴ ሲጮህብኝ ይሰማኝና መጽሓፉን አስቀምጬ እተኛለሁ ጧት ስነሳ መጽሓፍ ቅዱሱ መሬት ወድቆ የለበስኩት ልብስ ከላዬ ወድቆ አገኛለሁ ወይ አምላኬ አበድኩኝ እንዴ ራሴን ሳትኩ ማለት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

አንዳንዴ ሌሊት ሌሊት እነሳለሁ እወጣለሁ የት እንደሚሄድ አላውቅም የምኖረው 8ኛ ፎቅ ነው ወደ ታች እየተመለከትኩኝ ከእንቅልፍ እንደ ነቃ ሰው እነቃለሁ እደነግጣለሁ ወደ ቤቴ ስገባ እቤቴ እየጠፋብኝ ወደ ሌላ መንገድ ገብቼ መኪና ሁለት ጊዜ ሊገጨኝ እግዚአብሔር እየጠበቀኝ እተርፍ ነበር በስራዬ ቦታ ሁልጊዜ ሰላም የለኝም እበሳጫለሁ የሚነግሩኝን አልሰማም በየቀኑ የምሰራበትን ፓስ ወርድ ይጠፋብኛል ኮምፒተሩን ልከፍት ስል

**በገፅ 15 ይቀጥላል**

# ዜና ሮሆቦት

## ኮንፍራንስ

ከዲሴምበር 31 እስከ ጀነዋሪ 1 በተደረገው ኮንፍራንስ ፓስተር ጎሳዬ ከኢትዮጵያ ሙሉቀን መለሰ ደግሞ ከዋሽንግተን ዲሲ በመምጣት ለሶስት ቀናት በነበረው ኮንፍራንስ ላይ አገልግለዋል።



## የእራት ስነስርዓት

በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ በፈንድ ሬዚንግ የሚያገለግሉ እህቶችና ወንድሞች የጌታ እየሱስ ክርስቶስን ልደት በዓል ምክንያት በማድረግ ለቤተክርስቲያኒቱ አባሎችና እንዲሁ ፈቃደኛ ሆኖ ለመምጣት ለሚፈልግ ሁሉ የእራትና የአምልኮ እንዲሁም ገቢው ለቤተክርስቲያን ህንጻ ግዢ እንዲሆን የጫረታና የዕቃ ሽያጭ ጊዜ አድርገዋል ይህንን በተመለከተ እህት አደይ አበበ ስለነበረው ዝግጅት የሚከተለውን አቅርባለች

የ2007 ገና በዓልን በማስመልከት ባህላዊ  የእራት ምሽት ተደረገ

ይህን የእራት ምሽት በሃላፊነት ያዘጋጁት የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን የህንጻ ግዢ ፈንድ ሬዚንግ ኮሚቴ እና ኢትዮጵያን ለ ኢትዮጵያውያን የተሰኘው የአግልግሎት ዘርፍ በመተባበር ሲሆን ዝግጁትም የተካሄደው  ዲሴምበር 15/2007 ሚኒያፖሊስ በሚገኘው ቤቴል ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበር።



የዝግጅቱ ዋና ዓላማ  በአሜሪካን ወላጆች ከኢትዮጵያ አዳብትድ ሆነው የመጡ ልጆችንና አሳዳጊ ቤተሰቦቻቸውን ከኢትዮጵያ ባህልና በዚህ ከሚገኘው ህዝብ ጋር ለማስተዋወቅ ሲሆን በወቅቱም ከትኬትና ከተላያየ ነገር ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ የቤተክርስቲያን ግዢ ለማካሄድ ለሚደረገው ለፈንድ ሬዚንግ ገቢ ለማድረግ ነበር። በመሆኑም በስፍራው እንዲገኙ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተለይም ከችልድረን ሆም ሶሳይቲ በኩል ከኢትዮጵያ ልጆችን አዳብት አድርገው የመጡ አሜሪካውያን ወላጆች ከነልጆቻቸው እንዲገኙ ተደርጓል። የቤተክርሰቲያኒቱ አባላትና ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው ተጋባዥ ኢትዮጵያውያን እንግዶች ተገኝተዋል።

በወቅቱ በቀረበው ዝግጅትም የኢትዮጵያውያንና የኤርትራውያንን ባህላዊ አለባበስ የሚያሳይ ፋሽን ሾ የቀረበ ሲሆን ስለነዚህ አገሮች ታሪካዊ ስፍራዎችና ስለ ህዝቡ አኗኗር የሚያስተዋውቅ በመረጃ የታገዘ ትምህርት ሰጪ ስላይድ ሾ ለዕይታ ቀርቧል። ከኢትዮጵያ አዳብት ተደርገው የመጡ ልጆችንም ከአሜሪካን ቤተሰቦቻቸው ጋር ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጳውያን በተሰኘው የአገልግሎት ዘርፍ በኩል የሚያደርጉትን ተሳትፎ ያካተተ ስላይድ ሾም ታይቷል።

ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ ጎሳዎች ባህልና ታሪካዊ ስፍራዎችን የሚያሳይ የፎቶግራፍና  አርት ኤግዝቢሽን ቀርቧል። በዕለቱም በነበረው የዕራት ዝግጅት ላይም ጣፋጭ የሆኑ ባህላዊ ምግቦች ቀርበዋል። በፕሮግራሙ ጣልቃም የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መዘምራን የተለያዩ ብሄረሰብ ልብሶችን በመ-ልበስ መንፈሳዊ ዝማሬን ያቀረቡ ሲሆን ህጻናትና ታዳጊ ወጣቶችም በበኩላቸው በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋ የጌታችንና የመድሃኒታችንን የእየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በማስመልከት ዝማሪዎችን አሰምተዋል።



በመጨረሻም የተለያዩ ባህላዊ አልባሳት፣ ጌጣጌጦች፣ የፎቶግራፍና የአርት ውጤቶች ለጨረታ ቀርበው ግዢ ተካሂዷል። ከጨረታውም ሽያጭም የተገኘው ገቢም ቀደም ሲል እንደተገለጸው ለቤተክርስቲያን ግዢ አገልግሎት ይውል ዘንድ በፈንድ ሬዚንግ ኮሚቴ አማካኝነት ወደ ቤተክርስቲያን ገቢ ተደርጓል።

## በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ጌታን እንደ ግል አዳኝ አድርገው የተቀበሉና የደህንነት ትምህርታቸውን የተከታተሉ 22 ሰዎች ተጠመቁ



በሚኒሶታ በምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ለሶስት ወራት በተከታታይ የተሰጠውን የደህንነት ትምህርት ተከታትለው የጠናቀቁ 22 ሰዎች ማርች 16/08 የውሃ ጥምቀት ወስደዋል። የጥምቀቱ ስነስርዓት የተካሄደው የዕለቱ መደበኛ ፕሮግራም እንደተከናወነ ሲሆን ስርዓቱን ለመከታተል የቤተክርስቲያኒቱ አባላትና ጥሪ የተደረገላቸው በርካታ እንግዶች በስፍራው ተገኝተዋል።



በዚሁ ዕለት የተካሄደውን የውሃ ጥምቀት ልዩ ያደረገው በተላያዩ ጊዜያት በቤተክርስቲያኒቱ ጌታን ተቀብለው ከተጠመቁት ወገኖች ባሻገር ከህጻንነታቸው ጀምረው በዚሁ ቤተክርስቲያን በሰንበት ትምህርት በቃሉ ተኮትኩተው ያደጉ ለጋ ወጣቶችም መገኘታቸው ነበር። እነዚህ ወጣቶች ምንም እንኳን የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ልጆች ይሁኑ እንጂ ይህንን ስርዓት ሊፈጽሙ የቻሉት ጌታን እንደ ግል አዳኝ አድርገው በመቀበልና የደህንነት ትምህርት ተከታትለው በማጠናቀቃቸው ነበር። የጥምቀቱ ስርዓት በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ እንደተጠናቀቀም የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ ፓስተር እንድርያስ ሓዋዝ ስለተጠማቂዎቹ እግዚአብሔርን አመስግነው ቀሪ የህይወት ዘመናቸውን በጸሎት ለጌታ አሳልፈው ከሰጡ በኋላ አጠር ያለ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከዚያም ጌታን ከተቀበሉ በኋላ በህይወታቸው ያዩትን ለውጥ በማስመልከት አራት ወጣቶች ምስክርነት የሰጡ ሲሆን አንዲት እህትም ጌታ በህይወቷ ያደረለገላትን በተለይም ከተጠመቀች በኋላ ያየችውን አስደናቂ ለውጥ መስክራለች።



ከወጣቶች መካከልም ሁለቱ በግጥም መልክ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን አንዲት ወጣትም በበኩሏ ጌታ የሰጣትን ዝማሬ አሰምታለች።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ተጠማቂዎቹ ከልጅነታቸው ጀምሮ አብረው በቤተክርስቲያን በተለያየ ጊዜ ሲያካሂዱ የነበሩትን እንቅስቃሴ የሚያሳይ ስላይድ ሾዎ ከታየ በኋላ አንድ በጣም አስደናቂ ምስክርነት በቪዲዮ ቀርቦ እይታ ላይ ውሏል። ታሪኩ ያተኮረው በክርስቲያኖች ጸሎት ምክንያት እግዚአብሔር ከ3 ቀን በኋላ ከሞት ስላስነሳው ሰው ሲሆን ይኸው ሰው ሞቶ ከተነሳ በኋላ ሞቶ በነበረበት ወቅት ስላጋጠመው ሁኔታ በዝርዝር ተብራርቷል።

በመጨረሻም በዕለቱ በአንድነት ለመቁረስ የተዘጋጀውን ማዕድ በህብረት በመቁረስ የአንድነት ጊዜ ተደርጓል። በተለይ በዚህ ቀን ማለትም በተጠመቀችበት ቀን የልደት በዓሏን ያከበረች ወጣት ስለነበረች ለርሷና ለተጠማቂዎቹ ወጣቶች የተዘጋጀውን ኬክ እንዲቆረስ ተደርጓል በዝግጅቱ መጨረሻም ቤተሰቦች ለተጠማቂዎቹ ያዘጋጁትን ስጦታ በመስጠት የዕለቱ ፕሮግራም ተጠናቋል።

## የእልልታ ኮንፍራንስ



በፓስተር ቶሎሳ ጉዲና ራዕይ መሰረት ከማርች 28-30 ድረስ የኢትዮጵያውያንና የኤርትራውያን ቤተክርስቲያናት በአንድ ላይ ሆነው ለሶስት ቀናቶች ኮንፍራንስ ያደረጉ ሲሆን በዚሁ ቀንም ፓስተር ቶሎሳ ጉዲና ስለ እልልታ አስተምረዋል። ከየቤተክርስቲያኒቱም የተውጣጡ መዘምራን መዝሙሮችን አቅርበዋል።

# ድ ብ ቅ  እ ን ባ ዎ ች

የአጭር አጭር ልቦለድ
ከስንታየሁ

ፌብረዋሪ 2008
ኦሊቭ ጋርደን ሬስቶራንት
ብሉሚንግተን ሚኒሶታ

የሚኒሶታን የምሽት ቅዝቃዜ ተቋቁማ ከሆቴሉ ቅጥር ግቢ የደረሰችው ከቀጠሮችዋ ሰዓት ጥቂት ዘግይታ ነበር፡፡ የመኪናዋን ሞተር ካጠፋች በኋላ በሩን ቆልፋ በቀጥታ ወደ ምግብ ቤቱ አቀናች፡፡ በስሱ ከሰማይ የሚወርደው በረዶ ምሽቱን ድምቀት ችሮት ነበር፡፡ ተንጠልጣይ የግድግዳ ላይ አበቦች ያስዋቡትን ጠባብ ኮሪደር በመንተራስና የመጠጥ ባሩን ወደ ግራ በመተው ወደ መመገቢያው ክፍል ዘለቀች፡፡ ከጥቂት ጥንዶች በስተቀር  በውስጡ እምብዛም ተመጋቢዎች የማይታዩበትና የጣሊያን ሃገር ተወዳጅ ምግቦች የሚቀርቡበት የምግብ አዳራሽ ደብዘዝ ባሉ የሻማ ብርሃንና በጸጥታ ድባብ ተውጠዋል፡፡ በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ለስላሳ ሙዚቃ በእድሜ ገፋ ካለችው አስተናጋጅ ጋር ቤቱ ተቀበላት፡፡ ወዲያውኑ ከዮናሴ አጠገብ ራስዋን ተቀምጣ አገኘችው፡፡

ለብዙ ጊዚያት ሞክራ ያቃታት ጸልያም ለውጥ ያላየችበትን የዮናስ ያልተለመደ ባህርይ ለመቀየር ዛሬም አልሰነፈችም፡፡ ብዙ ያደምጥ እንደሆነ እንጂ በፍጹም አለማውራቱ ሰርክ ያበግናታል፡፡ ግን አንድም ቀን ስለ ራሱ አውርቷት የማያውቀው ስለምንድነው? ከቀናት በአንዱ ይህንኑ ጥያቄ ብታቀርብለት ምን ብሎ እንደመለሰላት አስታወሰች ክርስቲያን መሆኔን ነው የማውቀው ያላት፡፡

በፊታቸው ስለቀረበው ማዕድ ለማመስገን አንገቶቻቸውን ዝቅ በማድረግ አይኖቻቸውን ጨፈኑ፡፡ በጨረፍታ አሻግራ ተመለከተችው ከጸጉሩ ጋር ተያይዞ በቀጭን ቅርጽ ወደ አገጩ ከሚወርደው ጸጉሩ በስተቀር ጺሙን ሙልጭ አድርጎ ተላጭቶታል፡፡ ሙልት ያሉት ጉንጮቹ የታረሰ ከሚመስለው ሰፊ ግንባሩ ጋር ተደምረው ግርማ ሞገስ ሆነውታል፡፡ የምትወዳቸውን አይኖቹን ማየት ባለመቻሏ ተቆጨች፣ በምስጋና ጸሎት መካከል " የአብርሃምና የሳራን ማዕድ እንደ ባረክህ… " ሲል አደመጠች፡፡ የእርሱ ሳራ መሆንን አጥብቃ ስትመኝ ጸሎቱን በ "አሜን" አሳርጎ አንገቱን ቀና አደረገ፡፡ ህይወት አልባ ፈገግታ ከፊትዋ ቢያነብም በዝምታው እንደጸና ቃላት ሳይለዋወጡ ራታቸውን መመገብ ቀጠሉ፡፡

"ዝምታ ወርቅ ነው!" አለ ምስኪን ያገሬ ሰው፡፡ "እውነቴን ነው የምልህ ዮናሴ ያንተ ግን በዛ፡፡ የመቃብር ያህል ከፋ! ዝምታ እኮ ይኮሰኩሳል ውበትን ያጨልማል፡፡ ፈገግታን ነጥቆ በምትኩ ጽልመትን ያወርሳል ለእኔ ያለህን ፍቅር እዚያ ውስጥ እንድትገድልብኝ አልፈቅድልህም የእኔ ውድ ታስፈልገኛለህ፡፡ የትላንት የህይወት ምዕራፍህን በቃላት ግለጽልኝ፡፡ እያደመጥኩኝ ነው!" ምሬት ለተቀላቀለ ጥያቄዋ መልስ ስትጠብቅ ደቂቃዎች ነጎዱ፡፡ እርሱ ግን እንዳችም አልተናገረ፣እንደበቱ እንደተለጎመ ህመምተኛ በዝምታው ውስጥ ጠፋ፡፡

"ሠርክ አጠገብህ ተቀምጬ እስከመፈጠሬ ትረሳኛለህ፡፡ ያንተ ፊደል መቁጠርና አረማመድህን ከጌታ ጋር ማድረግህ ያስተማሩህ ይህንን ነው? ዮናሴ የማትፈልገኝ በህይወትህም ውስጥ ረብ የላትም ብለህ የምታሰብ ከሆነ አሁኑኑ ንገረኝ!! ዝም አትበል! አፍህን ተናገርበት!" ቁጣዋ ማየሉን ከመጤፍ ሳይቆጥር ከፊት ለፊት የቀረበውን ውሃ ተጎነጨ፡፡

ከወትሮው ባልተለየ መልኩ ከዝምታው መካከል ተሸጉጦ በስስት ሁለመናዋን ተመለከታት፡፡ ምድረ አዳማትን ያንበረከከ ውበትዋ ስለምን ከእርሱ ህይወት ዋጋ እንዳጣ ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ በመፈቀሩ ልቡ በኩራት አብጦ አልነበረም፡፡ ውበትና ደምግባት ከንቱነታቸውን ከመጽሓፍ ቅዱስ መረዳቱም አልነበረ ግን ወደ ህይወትዋ እንዳይገባ ሰቅዞ የያዘው ያልተቆጨ የትናንት ጥቁር ምዕራፍ ነበር፡፡ ብኩርናውን በምስር ወጥ እንደለወጠው
ኤሳው እርሱም ዝምታውን በእርሷ ፍቅር ቢለውጥ ተመኘ፡፡ ከራሱ ጋር ብዙ ተሟገተ፣ አፈርሳታ ቆመ በስተመጨረሻው በዝምታው ተረታ፡፡ ደቂቃዎች ነጎዱ…

ከዓይንቿ ቁልቁል የሚወርዱት የእንባ ዘለላዎች እንዲራራላት ስላስገደዱት የእጁን መዳፍ ወደ ፊት ላከ፡፡ ከመቅጽበት ወደ ኋላ አፈግፍጋ "እንዳትንካኝ" ስትል ጮኸች፡፡ "ቢገባህ ልብህ እንጂ የእጆችህ መዳፍ ምን ይጠቅሙኛል?" አፍታም ሳትቆይ ንግግሯን ቀጠለች፡፡ "በእንባ ማበሻ ሶፍት ወረቀትና በእጅ መዳፍ መካከል ያለው ልዩነት ይገባሃል? ጊዜዬን በከንቱ እያባከንሁ እንደሆነ አሁን ገባኝ ፡፡ በቃ ግኑኝነታችን ስህተት ነበር፡፡ ነገሮቻችንን እዚህ ጋ እንቋጭ!!" የእጅ ቦርሳዋን ከጠረጴዛው አንስታ ከመቅጽበት ብድግ አለች፡፡ የአንገት እስከርፎዋን እያስተካከለች ኮትዋን ከባለዩ ደርባ ጥቂት ተራመደች፡፡ ዞራ ተመለከተችው፡፡ ጀርባው በግልጽ የሚታያት ዮናስ ለመዞር እንኳ ሙከራ አላደረገም፡፡ እልህ በመላው ደምስሯ ሲዘዋወር ተሰማት፣ለመጨረሻ ጊዜ "ጌታ ይባርክህ!" ስትል ጮሃ ተናገረች፡፡ ምጸት የሚመስለው ምርቃቷ ወዲያው በቤቱ የጸጥታ ድባብ ውስጥ ሰጥሞ ቀረ፡፡ የእግር ኮቴዋ ድምጽ እየራቀው ሲሄድ አደመጠ፡፡ እረፍት ሽል ይመስል በውስጡ ሲገላበጥ ተሰማው፡፡

ከደቂቃዎች በፊት መዓዛ የነበረችበትን ባዶ ወንበር ቀና ብሎ ተመለከተው፡፡ እርሷ ብትሄድም ጥያቄዎቿና ጀምራ የተወችው ምግብ ከፊቱ ነበሩ፡፡ ሊከተላትና ይቅርታ ሊጠይቃት አልወደደም፡፡ ምን ያህል በህይወትዋ ዋጋ እንደከፈለ አላወቀችም ነበር፡፡ የሚቀፍ ታሪኩን ቢተርካት አለመውደዱ ጥፋት አልነበረም፡፡ እንኳንስ እርሱ ምሽቶቻችንን ምታደምቅልንን የጨረቃ ጀርባ ማን አይቶ ያውቃል? አነሰም በዛ እያንዳንዳችን የየራሳችን ጥቁር የጀርባ ታሪክ አለን፡፡

ከዓይኖቹ ጥጋጥግ የተንጠለጠሉ ጤዛዎች የሚመስሉ እንባዎቹ ቁልቁል ሳያቋርጡ ይወርዱ ጀመር፡፡ የፊት ማበሻ ሶፍትም ሆነ የእጅ መዳፍ አልፈለገ፡፡ በምትኩ ከኮት ኪሱ ውስጥ ትንሽ ብልቃጥ አውጥቶ ከፍቶ ሁለት የዕድሜ ማራዘሚያ እንክብሎችን ውጦ በውሃ ካወራረዳቸው በሁዋላ አይኖቹን ጨፈነ፡፡ ጥቂት ቆይቶ ወጥቶ ሄደ፣

## ከጠላት እስራት...

ከገጽ 11 የቀጠለ

አታምኑኝም ስሜን እስፔል ማድረግ ይጠፋብኛል ስራ ላይ በጣም አስቤ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ እርዳኝ ብዬ ስራዬን እጀምራለሁ በቃ ምንም ጤና ሰላም የለኝም ይህ በእንዲህ እያለ ሶስት ዓመት ሆነኝ በአሜሪካ ውስጥ ይገርማችኋል እግዚአብሔር ሊያኖር ሲል ብዙ ተዓምርን ያሳያል እንኳን በህይወት ማኖር አይደለም ከመቃብር ያስነሳ የሞተ የሸተተውን እሬሳ ጌታ ያስነሳ እና እኔንም ህይወትና ዕድሜ የጨመረልኝ አምላክ ነው።

ወደ ጌታ ለመምጣት ልቤ ተነሳሳ ይህ ሁሉ የሚያደርግልኝና የሚጠብቀኝ ልጁ እየሱሰ አይደለም እንዴ የፈሰሰው ደሙ የተወጋው ጎኑ የቆሰለው ለሰው ልጆች ደህንነት አይደለም ብዬ ልቤ ተነሳሳና ቤተክርስቲያን ልሂድ እህቶቼን ውሰዱኝ ብዬ ተነሳሁ አላመኑኝም በደስታ ሲሮጡ መጡ ትንሿ እህቴ ነይ ውሰጂኝ ብዬ ደውዬላት ልክ መንገድ እንደ ጀመረች ግማሽ ሰዓት ነድታ ደውዬ በቃ ሃሳቤን ቀይሬአለሁ አልሄድም አልኳት ለምን ስትለኝ በከፍተኛ ራስ ምታት የበላሁት ሁሉ እየወጣ መቆም አልቻልኩም ስለዚህ እዛ አስቸግርሻለሁ ብዬአት እንዳትመጣ ከለከልኳት የዛን ቀን ኮንፍራንስ ነበር ፓስተር ሰይፉ መጥተው ነበር። ለካ የዚያን ጊዜ የጌታ ስም የመድሃኒት የእየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠርቶበት አጅሬ መግቢያው ጠፍቶት በጭንቅላቴና በልቤ እያስጨነቀኝ አሳደረኝ።

ሌሊቱ ሁሉ በጭንቅ አልፎ እንደገና ደውዬ ዛሬስ እሄዳለሁ ብዬ በእግዚአብሔር ሃይል ሄድኩ ቤተክርስቲያን እንደደረስኩ እግሬ ተንቀጠቀጠ ሰውነቴ እንዳለ ይረብሸኛል ገብቼ በእህቶቼ መሃከል ተቀመጥኩኝ ሲመለክ ለኔ ጭንቅ ነበር ልቤ ይመታል ጭንቅላቴ ይጮሃል ሲዘመር ጆሮዬን ድፍት ብዬ እይዛለሁ ምክንያቱም ይጮህብኛል እንዲህ እያለ ዜማ አብቅቶ ፓስተር ሰይፉ አስተምረው ሲጨርሱ እንግዲህ ይህ ሁሉ የሆነው በእግዚአብሔር ልጅ በእየሱስ ክርስቶስ ነውና ዛሬ ብሞት ወዴት እንደሚሄድ አላውቅም ህይወቴን ለጌታ አሳልፌ እሰጣለሁ ጌታን እንደ ግል አዳኝ አድርጌ እቀበላለሁ የምትሉ ወደዚህ ኑና ይጸለይላችሁ ሲሉ እኔ ሁሌ እመጣለሁ እሄዳለሁ ግን ዛሬ ምነው ተረበሽሁ አልኩና እጄን ላውጣ ብዬ መለስኩት ሁኔታዬን የምታየኝ እህቴ ጸሃዬ ለምን አትሄጅም አለችኝ ፈራሁ አልኳትና ከትንሽ ደቂቃ በኋላ እጄን ሳወጣና ሳገባ ይመለከቱኝ ኖሮ ፓስተር ሰይፉ አይተው አንቺ ልጅ ነይ አሉኝ እኔ በዛን ሰዓት በጭንቀት ነበርኩና ዝም ብዬ ቁጭ አልኩና ወዲያውኑ ተነስቼ ለመሄድ ስቆም መብራት ሁሉ እንደጠፋና ፊልም ላይ የገባሁ መሰለኝ ጨለመብኝ የሆነውን አላውቅም።

ወደ ቤቴ ገብቼ እንቅልፍ ግጥም አድርጎ ይዞኝ ወደ አስር ሰዓት የሚሆን ተኛሁ እህቶቼ ብዙ ደጋግመው ቢደውሉ እንኳን አልሰማኋቸውም፤ ፤ እንዲህ እያለሁ በየጊዜው ቤተክርስቲያን ደጋግሜ መሄድ ጀመርኩ ውስጤ የጌታ ፍቅር አደረብኝ በቃ ስሄድ እሱን የማየው ይመስለኛል ግን ገና በሩ ላይ ስደርስ ይጨልምብኛል ብዬ ለእህቴ ለሚሚዬ ነገርኳት ከዚያ ወንጌላዊ ዮሃንስ ይጸልይልሻል ስትለኝ እሱ ማነው እኔ እራሴ ጸልዬ እድናለሁ ሁለተኛ እንዳተነሽብኝ እሱን ሰው ብያት ትዝ ይለኛል ሙሉ ቀን ስልክ ስትደውል ዘግቻት እንደ ነበር። ይገርማችኋል ልክ እሁድ ሲመጣ ጭንቅላቴ ይረበሻል ነገ ቤተክርስቲያን ለመሄድ ማታ ሲደውሉ እኔ ሰላም የለኝም እጨነቅና አድራለሁ ልክ አምልኮ ሲጀመር እኔ እጨነቃለሁ ወንጌላዊ ዮሃንስ ገና መድረክ ላይ ሲወጣ ልክ ሌባ ፖሊስ ሲመጣ እንደሚሸሽ ልሸሽ ሽንቴ እንደመጣብኝ እወጣለሁ ከዛ በመከራ እገባለሁ ይህ በእንዲህ እንዳለ የደህንነት ትምህርት ሲሰጥ እከታተላለሁ።

ትምህርቱን ልክ እንደጨረስን አንድ እሁድ ቀን በእህት ጽጌረዳና በአደይ የተሰጠውን የደህንነት ትምህርት ጨርሳችኋል አሁን ደግሞ ወንጌላዊ ዮሃንስ መጥቶ ይጸልይላችኋል ብላ አደይ ሰትናገር ምነው ይህ ሰው ባይመጣ ብዬ ተበሳጨሁና አደይን በቃ እኔ ውጪ ልውጣና ልጠብቃችሁ አልኳት አይ ቆይ እዚህ ቆይ ስትለኝ ልቤ ትመታ ጀመር ከመምጣቴ በፊት ማታ ሌሊቱን ሙሉ በህልሜ ተኝቼ ስጨነቅ በቃ መሄድሽ ነው ልታመልጪኝ ነው እያለ ይሚገተኛል ምንድን ነው እያልኩ ሁሌ የሞቱት ዘመዶቼ ነበሩ የሚታዩኝ በቃ ልትለይን ነው ይሉኛል እኔ ምንም መልስ አጣለሁ ለካ አጋንንቶች ነበሩ የሚከራከሩኝ እሱ ሲመጣ ልቤ የሌሊቱን እያሰብኩ በቃ እሱ ከጸለየልኝ የምሞት መሰለኝ እና ገና ወደ እኔ ሲመጣ እጁ አታምኑኝም እንደ እሳት አቃጠለኝ እንደ ጋለ ብረት እጁ ጭንቅላቴን ሲነካኝ ተሰማኝ ከዚያ ወደኩ ምን እንደሆንኩ አላወኩም ያን ጊዜ እግዚአብሔር ከጠላት እስራት ነጻ አወጣኝ።

ለመጠመቅ አንድ ቀን ሲቀረኝ ይህ ነው የማይባል ጭንቀት ለቀቀብኝ በቃ እዛው ውሃ ውስጥ ይሆናል የኔ ህይወት የሚያበቃው ብዬ ፈራሁ ግን ጌታ አይዞሽ ጌታ ሊያድንሽ እንጂ ያንቺን ህይወት ሊነጥቅ አይመጣም የሚል ቃል በአእምሮዬ መጣብኝ።

በማግስቱ ወደ ጥምቀቱ ቦታ ሄድኩኝ በፍርሃት ነበርኩ አሁንም እህቶቼ መፍራቴን ሲያዩ አጽናንተውኝ አይዞሽ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው አሉኝ። እኔም እግዚአብሔር እንዳደረከኝ አድርገኝ ብዬ ወደ ጥምቀቱ ገባሁ ተጠምቄ ከመውጣቴ በፊት ውሃ ውስጥ እያለሁ ምን ልበላችሁ የተሰማኝ ደስታ ውሃ ውስጥ ሲያስገቡኝ ልክ ገነት እንደገባሁ ያህል ባላስወጡኝ ብዬ ደስ የሚል ህልም ውስጥ ያለሁ ነበር የመሰለኝ ሰውነቴ ሁሉ ያበራ ነው የመሰለኝ ወዲያው እንደተጠመኩና እንደወጣሁ በደቂቃ ውስጥ እናንተ እራበኝ አልኩኝ አደይና ጽጌረዳ ሳንድዊች አምጥተውልን ነበር ብሉ አሉን እሺ ብዬ አንስቼ በላሁት ድሮ ቀዝቃዛ ሳንድዊች አልበላም ከአምስት ደቂቃ በኋላ እህቶቼ የደስታ አበባ ሰጥተውኝ አበባውን ይገፔ በቃ እኔ ብቻ የእግዚአብሔር ልጅ የሆንኩ መስሎኝ ኩራት ተሰማኝ በቃ ይሄ ነው የማይባል ደስታ ተሰማኝ እንደገና ራበኝ አሁን ምሳ እንብላ ስል እህቶቼ የደስታ ሳቅ ሳቁብኝና ወደ አበሻ ሪስቶራንት ሄድን በቃ እዛ ሪስቶራንት ቢያንስ ሁለት ምግብ ያህል ይሆናል ተርቦ እንደ ቆየ ሰው በላሁ፤ ፤ ከዚያ የብርጭቆ ውሃ ከሃያ ዓመት በፊት ይሆናል የጠጣሁት እና አምጪ እጠጣለሁ ብዬአት ግጥም አድርጌ ጠጣሁት እህቶቼ በቃ በእግዚአብሔር ስራ ተደንቀው መጮህ እስከሚያቅታቸው እየጮሁ ነበር የሚስቁት ሰዎች ሁሉ እየተገረሙ እነዚህ ጴንጠዎች እንዲህ እስኪ ሰማ ድረስ ምን ይጮሃለሁ ብለው ያዩን ነበር እኛ ግን እግዚአብሔር በሰራው አስደንቆንና አስደስቶን ለረዥም ጊዜ ሳቅን እልል አልን ጌታ ስራውን ማዳኑን መፈወሱን ስላሳየን ሳቅን እግዚአብሔርን አመሰገንን።

እናንተ የምትበሉትን የምትጠጡትን ውሃ፤ ወተት፤ ቅቤ እንደ ልቤ መብላት መጠጣት ቻልኩኝ በጌታ በእየሱስ መፈወሴ ደስ እያሰኘኝ በህይወቴ ሁሉ ስላስደሰተኝ አሁን ከአስፈራራኝ ቤት ወጥቼ ከ ሁለት ልጆቼ አንድ የራሴን አንድ የእህቴን ልጅ ጋር በደስታና በህይወት ምግቤን እየበላሁ እየጠጣሁ እኖራለሁ፤ ፤ እኔን እንደ ሰማኝ እናንተንም የህይወት እንጀራ ይስጣችሁ ጌታን ከአገኘሁ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ሆኖኛል እድሜዬ ቀጥሎ ኑሮዬ ተስተካክሎ ከጌታ ጋር ደስ ብሎኝ እኖራለሁ።

እግዚአብሔር ይመስገን ይቺን ቀን አሳይቶኝ ለመመስከር ስለአበቃኝ ጌታ ይባርካችሁ። ስለ ኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያንም እግዚአብሔር ይመስገን እግዚአብሔር እንድንበትና እንፈወስበት ዘንድ ስለ ሰጠን ቤተክርስቲያን ይኸው ዛሬ ያለገንዘብ ታክሜ ወጣሁ እግዚአብሔር ውለታ የዋለልኝ ሴት ነኝ። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን አሜን!!!

እህታችሁ ጻሓይ ወልደየስ

# የሰው ተፈጥሮ ባህርይ

## Temperament

(ካለፈው የቀጠለ)

## ብርቱ ኮለሪክ (Powerful Choleric)

ባለፈው ጽሑፍ በባህርያቸው በሜላንኮሊ (Melancholy) የሚጠቃለሉትን ሰዎች ተመልክተናል:: አንድ ሰው ከባህርያቱ በአንዱ ይመደባል ሲባል ከሌሎቹ ሦስቱ ባህርያት ውስጥ የለበትም ማለት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት:: ዋናው ሀሳብ የትኛው የባህርይ ዓይነት ጎልቶ ይታያል ነው:: እኛ የተለያዩ ባህርያት ቅይጦች ስንሆን ነገር ግን አንዱ ዓይነት ባህርይ ተፅኖ በማድረግ ከሌሎቹ ይልቅ አጉልቶ ለሌሎች ያሳየናል::

በዚህ ጽሑፍ የምንመለከተው ይህቺ ዓለም በብዙ የሚያስፈልጓትን በኮለሪክ የተፈጥሮ ባህርይ የሚመደቡትን ሰዎች ይሆናል::

**ኮለሪኮች:--** (1) በራሳቸው ሁኔታ ዙሪያ ያልተወሰኑ (the extroverts) ናቸው (2) ሰራተኞች፣ አድራጊዎች (the doers) ናቸው (3) ከነገሮች (ከሁኔታዎች) መልካም ነገርን የሚጠብቁ (the optimist) ናቸው::

ኮለሪኮች ነገሮችን በቁጥጥር ሥር የማደረግ ችሎታ አላቸው፣ ባልጠራና አወዛጋቢ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ውሳኔዎችን በድፍረት ይወስናሉ፣ ጠንካራ የአመራር ችሎታና ሥልት አላቸው:: በአጠራጣሪ ሁኔታ ውስጥ አንድን ነገር ለመሞከር ፈቃደኞች ናቸው:: በዕውነት ላይ ይቆማሉ፣ በማይመስል ወይም በሚያስቅ ሁኔታ ውስጥ እንኳን ቢሆን ግድ የላቸውም:: በራሳቸው ይተማመናሉ፣ የሕይወት መመሪያ አላቸው:: ችግሮችን ለመዋጋት ፈጣኖች ናቸው::

ብርቱ ኮለሪኮች ታታሪዎችና የማይቻል የሚመስልን የሚያልሙና የማይደረስበትን ለመድረስ የሚሞክሩ ናቸው:: ሁልጊዜ ያልማሉ፣ ይደርሳሉ፣ ያከናውኑማል:: በተፈጥሮ ካላቸው የመምራት ችሎታ ጋር በዓላማ ስለሚመሩ አብዛኛውን ጊዜ በመረጡት የሥራ ዘርፍ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛሉ:: በዚህ በአሜሪካ አብዛኞቹ የፖለቲካ መሪዎች ባህርይ በኮለሪክ ይመደባል::

**ኮለሪኮች**:-- (1) ለመሪነት የተፈጠሩ ናቸው:: ገና ከልጅነታቸው ሀላፊነት የመውሰድና ነገሮችን በቁጥጥር ሥራቸው የማድረግ ዝንባሌ ይታይባቸዋል፣ መብታቸውንም ጮክ ባለ ድምጽና በንዴት ይጠይቃሉ:: (2) ቸልተኞች አይደሉም:: ለውጥን ለማምጣት ያልተቆጠበ የውስጥ ፍላጎት አላቸው፣ ያልተስተካከለና ከቦታው ያልሆነን ነገር ለማስተካከል ግድ ይላቸዋል:: በገቡበት ቤት የተሰቀሉ ፎቶ ግራፎችን ያስተካክላሉ (በሄዱበት ቦታ ሁሉ ካለቦታው የሆነ ነገር አያሳርፋቸውም ማለት ነው)፣ ራሳቸውን መከላከል በማይችሉ ላይ የሚደረግን በደል ዝም ብሎ ማየት አይሆንላቸውም፣ እዲታረም (እንዲስተካከል) እርምጃ ይወስዳሉ:: ስለ መብት ጥያቄ ዘመቻ ለማድረግም ፈጣኖች ናቸው::

3) ቆራጥና በውሳኔአቸው ተፅዕኖ የማድረግ ችሎታ አላቸው:: ሌሎች ለውሳኔ በሚያቅማሙበት ወቅት ኮለሪኮች ወዲያው ይወስናሉ፣ ሁሉም ሰው ለችግሩ የወሰዱትን እርምጃ የሚያደንቅላቸው ባይሆንም ፈጥኖው መፍትሔ በመስጠት ጊዜን ከማባከን ያድናሉ:: መፍትሔ አሏቸው፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ፣ ፈጣን ውሳኔዎችንም የመስጠት ችሎታ አላቸው:: ነገር ግን ይህ እርግጠኝነታቸውና ልበ ሙሉነታቸው በአንዳንዶች ላይ በራስ አለመተማመንን ስለሚያመጣ እምብዛም ተወዳጅ አያደርጋቸውም:: የመምራት ችሎታቸውም በቀላሉ ዓለቃ ሆነው እንዲታዩ ያደርጋቸዋል::

(4) የውስጥ መተዳደሪያዎች ወይም መመሪያዎች (bylaws) ዕውቀት ባይኖራቸውም እንኳን ወዲያው በምንም ነገር ውስጥ ሀላፊነት ወስደው የመምራት የተፈጥሮ ችሎታ አላቸው:: ለሕይወት ገጠመኝ ችግሮች ተግባራዊ የሚሆን ምላሽ አላቸው::

(5) በዓላማ የሚኖሩ ስለሆኑ ሰውን ከማስደሰት ይልቅ በዓላማቸው ፀንተው ከግብ መድረስን ይመርጣሉ:: ሰዎችን ከመንገዳቸው ዞር ማድረግ ከቻሉ ሥራቸውን በተሸለ ሁኔታ ያከናውናሉ:: ነገር ግን ሳያውቁት ሌሎችም እነሱን መከተል ያቅታቸውና ራሳቸውን ብቸኛ ሆነው ያገኙታል::

(6)መመሪያዎቻቸውን የሚከተሉ ናቸው፣ ሌሎችም እንዲከተሉላቸው በግልጽ የሚያሳውቁና የተደራጁ ናቸው:: ለቀልጣፋና ተግባራዊ ድርጅት የተጠበቡ ናቸው፡፡

(7) ሥራን የማከፋፈልና የመወከል (delegation) ችሎታቸው ከማንም ይበልጥ ሥራን እንዲያከናውኑ ያደርጋቸዋል::

(8) ተቃውሞን አይቀበሉም፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም ቢሆኑ ሊሰሩ ያሰቡትን በብርታት በመጋፈጥ ያከናውኑታል:: በነቀፋና በተስፋ አስቆራጮች ሀሳብ ተስፋ አይቆርጡም፡፡ ዐይናቸው ሁሌ በግባቸው ላይ ነው::

(9) ጓደኛ ብዙም አያስፈልጋቸውም:: ማህበራዊ ስብስብን (socialization) ጊዜ እንደማጥፋት ይቆጥሩታል፡፡ ዓላማው ግልጽ ከሆነላቸው ግን በማህበሩ ውስጥ ለመሳተፍ ወይም ለመስራት ፈቃደኞች ናቸው::

(10) ስለ ሁኔታዎች እንዲረዱ ወይም ትርጉም የሚሰጣቸው የውስጥ የተፈጥሮ አንቴና አላቸው:: ስለ ተረዱት ነገር እርግጠኛ ሲሆኑ ያስታውቁታል:: አብዛኛውን ጊዜ ትክክል ናቸው::

(11) በአደጋና በአፋጣኝ ሁኔታዎች ውስጥ ልቀው (በልጠው) ይታያሉ:: ችግር ሲከሰት ፈጥነው በመነሳትና ሀላፊነት በመውሰድ ሁኔታውን አዲስ አቅጣጫ ያሲዙታል::

**በአመራር ጉድለት መንግስት ይወድቃል፤ የመካሮች ብዛት ግን ድልን እርግጠኛ ያደርጋል:: ምሳሌ 11፡14**

## የኮለሪኮች ችግሮች ምንድን ናቸው? መፍትሔውስ?

**ኮለሪኮች፣**

(1) የሚመቻቸው ሁኔታዎችን መቆጣጠር ሲችሉ ነው:: ነገር ግን ሁኔታዎች በቁጥጥራቸው ሥር መሆን ባይችሉ እንኳን ራሳቸውን ከማህበረሰቡ ሁኔታ ጋር ማለማመድ አለባቸው:: ውሳኔ መስጠት እንዲችሉ ለሌሎች ዕድል መስጠትም ይኖረባቸዋል:: እነሱ ሁኔታዎችን ባዩት መንገድ ሌሎች ማየትና መረዳት ካልቻሉ እነሱ ትክክል ሌሎች ግን ስህተተኞች ናቸው የሚል እምነት አላቸው::

ሁሉን ነገር በአጭሩና በተሸለ ሁኔታ መስራት ይችላሉ፣ ሌሎች ግን ፈጣን መላሽ ከሌላቸው በትዝብት ወደታች ይመለከቷቸዋል:: ይህ አስተያየታቸው (አስተሳሰባቸው) በሥራቸው ያሉትንና አብረዋቸው የሚሰሩትን ስነልቦና ይጎዳል (ያቆስላል):: የሌሎች ድክመትን ያለ ርህራሔ ይጫናሉ:: ሁሉም ሰው በእነሱ ፕሮግራም መነቃቃትና በሃሳቡ መነሳሳት እንዳለበት ይጠብቃሉ:: ነገር ግን የባህርያትን ልዩነቶችና ውበት ኮለሪኮች ቢገነዘቡ በፕሮግራማቸው የተለያዩ ሰዎችን በትዕግስት ማካተት ይችላሉ:: አለበለዚያ ብጤያቸውን በማሰባሰብ ሌሎችን መተው ሊገደዱ ነው:: በማግባባት ወይም ወደ ሀሳባቸው በማስገባት እና በማምታታት (manipulation) ሰዎችን የማሰራት ዜዴና ችሎታ አላቸው:: ይህ ግልጽነት የጎደለው የአሰራር ዘይቤያቸውን ሰዎች ሲነቁበት ግንኙነት ይሻክራል:: ጓደኞችና የንግድ ሥራ ሸሪኮችም አብረው ብዙ አይቆዩም::

(2) ሰውን አያያዝ አያውቁበትም:: ታጋሽነትን መለማመድ አለባቸው፣ ሁሉ ነገር በራሳቸው መንገድ ወዲያው ካልተሰራና ችግር ካለበት እንደ ውድቀት በመቁጠር አቅጣጫን ለመቀየር ይቻኮላሉ:: ሌሎች ከእነርሱ ጋር ለምን እንደማይሄዱ አይገባቸውም:: የእግዚአብሔር ቃል በያዕቆብ 1:4 ላይ “ምንም የማይጎድልባችሁ ፍጹማንና ምሉአን እንድትሆኑ ትዕግስት ሥራውን ይፈጽም” ይላል:: ይህ ትእግስት ማጣት ድክመት መሆኑን ቢገነዘቡ በቀላሉ ከሌሎች ጋር አብሮ መስራትን ይማራሉ:: ጭምቶች ደካሞች እንዳልሆኑ ያስገነዝባቸዋል:: ጥንካሬያቸውንና በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ የማከናወን አቅማቸውን የተበላሸ ግንኙነት ስንኩል እንዳያደርጋቸው የባህርያትን ልዩነትና ውበት ማስተዋል ቢችሉ ይጠቀሙበታል እንጅ አይጎዱበትም:: ባይጠየቁም እንኳን ለሁሉ አቅጣጫ ማሳየት ወይም ምክር መለገስ እንዳለባቸው ይሰማቸዋል:: ነገር ግን እስካልተጠየቁ ድረስ ምክርን ከራስ ጋር ማቆየት ይመረጣል:: ሁሉም ሰው ለተሰነዘረው አስተያየት ወይም ምክር አድናቆት ላይሰጥ ይችላል:: ሌላው ችግር የሚጨቁንን (bossy personality) ማንም አይወድም:: የበላይነት የሚሰማው ሰው ሌሎች እንደሚያዩት ራሱን አያይም::
ሌሎች እንዴት ሊቀበሉት እንደሚችሉ ሳያጤኑትና የሌሎችን ስሜት ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ የመጣላቸውን ሀሳብ ፈጥነው በመናገር ለሁኔታው መፍትሔ እንደሰጡ ያስባሉ፣ ሥራው መከናወኑ ላይ ብቻ ያተኩራሉ፣ ስለሌሎች ስሜት ብዙም ግድ አይላቸውም:: የጽሑፍ ማስታወሻን ለሰው ሲሰጡ ክብደት ለመስጠት ወይም ለማስጠንቀቅ በቃላቶች ወይም በዓረፍተ ነገሮች ሥር ያሰምራሉ፣ የቃለ አጋኖ ምልክት(exclamation marks) ይጠቀማሉ:: አቀራረባቸውን በማለሳለስና በትህትና ከሰዎች ጋር በመስማማት መሥራት ቢችሉ የፈለጉትን ውጤት ከማምጣት የሚገታቸው ነገር የለም:: በቁም ነገርም ቢሆን በቀልድ አከራካሪ ነገሮችን ይወዳሉ፣ ዓላማቸው በአሸናፊነት ለመውጣት ስለሆነ ይህም የማይደገፍ ባህሪያቸው ነው::

(3) ኮለሪኮችን ምክር መስጠት አስቸጋሪ ነው:: ተሳስቼ ይሆን የሚል ሀሳብ በውስጣቸው የለም፣ በግትር አቋማቸው ምክንያት ከሌላው ሰው ሃሳብ ጋር መስማማት የማይችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል:: ሌሎችም ትክክል ሊሆኑ እንደሚችሉ ቢያስቡ ግን መልካም ይሆንላቸዋል:: ሁሉን እናውቃለን ብለው ስለሚገምቱና ሁልጊዜም ትክክል እንደሆኑ ስለሚያስቡ ሌላውን ሰው ይቅርታ ለመጠየቅ ይቸገራሉ፣ ይቅርታ ማለትም እንደድክመት ይቆጥሩታል:: ሀቁ ግን እነሱም አልፎ አልፎ ሊሳሳቱ እንደሚችሉ ማመን አለባቸው፣ ይቅርታ ማለትንም መማር አለባቸው::

(4) ሁሌም በሥራ የተጠመዱ ናቸው፣ ጎበዝ ሠራተኞችና ከሌሎች የበለጠ ብዙ የመስራት አቅም አላቸው:: ነገር ግን ራሳቸውን ማሳረፍ አይሆንላቸውም:: ሁልጊዜ መስራት እንደሌለባቸውና ዕረፍት መውሰድን መማር አለባቸው:: ዕረፍት መውሰድ (vacation) ጊዜ ማጥፋት እንዳልሆነ ቢገነዘቡ መልካም ነው::

## ከኮለሪኮች ጋር እንዴት መስማማት ወይም አብሮ መሥራት ይቻላል?

(1) ኮለሪኮች ካፈጣጠራቸው መሪዎች ናቸው:: መሪ መሆንንም ይወዱታል:: ለሁኔታዎች ፈጣንና ተስማሚ መልስ በመስጠት ጠንካሮች ስለሆኑ ከእነሱ ጋር ለመሄድ ጠንካራ አቋም መያዝ ያስፈልጋል:: አስተሳሰባቸውና አካሄዳቸው የገባው ሰው ጠንከር ያለ አቋም መውሰድ ከቻለ አክብሮትን ያገኛል::

(2) በዚህ የበላይነት ወይም ተቆጣጣሪነት ባህርያቸው ምክንያት በቤት ውስጥ ለሚሰሩና ለሚታቀዱ ሥራዎች የትዳር ጓደኞቻቸውን ፈቃድና ሀሳብ ለማካተት አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል:: ስለዚህ ኮለሪክ የሆነ ባል ወይም ሚስት የትዳር ጓደኛን በጥሞና አድምጦ ስለ ሃሳቡ ወይም ዕቅዱ አመስግኖ የጥቂት ደቂቃዎች ጊዜን በመጠየቅ ግልጽ በሆነና በጠንካራ አቋም እንዲሁም በጓደኝነት ስሜት ሀሳብን መግለጽ ያስፈልጋል::

(3) የሌሎችን ስሜት ሳይጠብቁ ያሰቡትን ወዲያው የሚያደርጉት ሌላውን ለመጉዳት አይደለም::
የሚያደርጉት ሆን ብለው ለጉዳት አለመሆኑን ከተረዳን አስተያየታቸውንና ሀሳባቸውን ያለመናደድና በትዕግስት የመቀበል አቅም ይኖረናል::

(4) በቤተሰብ ውስጥ የሥራ ድርሻ ክፍፍል ያስፈልጋል:: ኮለሪኮች ተግባራዊና ግልጽ በሆነ እቅድ ላይ መስራትን ይፈልጋሉ:: የሥራ ድርሻ ግልጽ ካልሆነ ግጭት ይፈጠራል::

(5) ኮለሪኮች ገና ከልጅነታቸው በተፈጥሮአቸው ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ብልሃት አላቸው:: ለውሳኔ ብንቸገር ወይንም በሃሳባችን በመንታ መንገዶች ላይ ብንሆን ኮለሪኮችን እንከተል ወይም ምክር እንጠይቅ::

ኮለሪኮችን በጎ ባልሆነው ባህርያቸው ጉዳይ ላይ መክሮ ማሳመን ከተቻለ ለመለወጥና ለመሻሻል ጊዜ አይወስድባቸውም:: ምክንያቱም በዓላማ ላይ የተደገፉ ስለሆነና ማንኛውንም ነገር ማሸነፍ እንደሚችሉ ለራሳቸው ለማስረገጥ ሰለሚፈልጉ ወዲያው እርምጃ ይወስዳሉ::

(ይቀጥላል)

ከታምሩ

## እረ እኮ አይረሳም

በንስር ክንፍ ተሸክሞ
ጠላቶቻችንን በባህር ስጥሞ
እዚህ አድርሶናል ጠላትን አባርሮ
ታዲያ! ስተኛ ስነሳ ስሙ እየናፈቀኝ
በቀትር በሌሊት ቃሉ እያግረኝ
አምላኬን ሳልጠራ መኖር ተሸነፍኩኝ
ጠገን ለአጥንቴ ፈውስ ለስጋዬ
የህይወቴ መሰረት ነው መደምደሚያዬ
ከቶ የማልሰጋበት ይከዳኛል ብዬ
አሁንም ዘላለም መተማመኛዬ
ዘወትር ምርጫዬ  ሁሌ መመኪያዬ
ኢየሱስ ብቻ ነው የዘወትር ኑሮዬ
ነፍስም አልቀረልኝ በፍቅሩ ቀለጠኩኝ
ከእርሱ ጋር ተሳሰርኩ ከእርሱ ተጣበኩኝ
እባኮውን ይተው!! ሁልጊዜ ከቀኑ አጥንቶ ይነቅዛል
እንደ ዱቄት ሆኖ ተበልቶ ያልቅሎታል
ያለ ምንም ድጋፍ ስጋ ብቻ ይቀራል
ይህ ባዶነት ደግሞ ችግርን ያመጣል
በወንድሞችና በህቶች መካከል ጸብን ይበትናል
በውስጦ እያደገ ፍሬውን ያፈራል
እነ መለያየት ወሬ ሓሜትኝነት
ቂም ይዞ መዋሸት ይቅር አለማለት
የውሸት ሰላምታ የውሸት ፈገግታ
ከልብ ያልሆነ የጥርስ ብልጭታ
ተመሳስሎ መኖር የዓለም ፋገራ
አሁኑኑ ያፍርሱ ቤቷን ሳትሰራ
የምስራች አለኝ እጅግ የሚያስደንቅ
ከአቤል ደም ይልቅ
እጅጉን የሚበልጥ እጅጉን የሚልቅ
ሓጢያትን ክፋትን በአንዴ የሚያስለቅቅ
የኢየሱስ ደም አለ አጥቦ የሚያጠራ
ምህረቱ ብዙ ታላቅም ነውና
በአምላክ እጅ ይወደቁ መሓሪ ነውና

ከድራማ አገልግሎት
ትዕግስት ጥላሁን

## የእግዚአብሔር ምህረት

እግዚአብሔር አስቦ ቃልን ተናገረ
በአምሳሉ በመልኩ ሰውንም ፈጠረ
ምድርን እንዲገዛ ሃላፊነት ስጠው
እንዲያስተዳድርም እንዲኖር እንዳሻው
ሁሉ ተፈቅዶለት እየኖረ እያለ
አንዲት ነገር ብቻ አትንካ ተባለ
ፈቃዴን ማክበርክን ለኔ መገዛትክን
ማረጋገጫና ምልክት እንዲሆን
ይቺን ብቻ አትንካ እንዳሻህ ሌላውን
አዳም አዳመጠ የአምላኩን ትዕዛዝ
ሊጠብቅ ሞከረ እንዳይመጣ መዘዝ
ነገር ግን ቆይቶ ትዕግስቱ ተፈታ
በእባብ ማባበል በሄዋን ውትወታ
ፈቃዱን ፈጽሞ በኋጢያት ተረታ
ፍርዱም ተፈጸመ እንዲሆን ከርታታ
እግዚአብሔር መሃሪ ስራውም ታላቅ ነው
ሰውን ወደራሱ ሊያቀርበው አሰበው
የዘላለምን ህይወት ዳግመኛ ሊሰጠው
ወደ ፍቅሩም መንግስት ጨርሶ ሊያስገባው
መድሃኒት ከፍጥረት ቢፈለግ ቢታጣ
እግዚአብሔር ከራሱ ከክንዱ አወጣ
ማንም ባላሰበው ባልጠበቀው ዓይነት
ጾጋ እውነትን ለብሶ ተሞልቶ በብቃት
ዓመጻንም ሽሮ ጽድቅን ሊመሰረት
ከሰው ተወለደ የዓለም መድሃኒት
ሰይጣን ተናደደ ውሉም ግራ ገባው
እንዴት እንደሚያከሽፍ መፍትሄ ቢጠፋው
አስታወሰ አሰበ የቀድሞ ስራውን
ጻድቃንን ያረደው ነፍሰ ገዳይነቱን
ገና ከጅምሩ ህጻኑ ሲወለድ
ሊገለው ሞከረ እሩቅም ሳይኬድ
እንዳያሸንፈው በብርቱ በከባድ
እግዚአብሔር ቀደመው ወጥመዱ ከሸፈ
ህጻኑም አደገ ክፉውን አለፈ
የዲያብሎስ እቅድ በፍጹም አልሰራ
ማድባት ማሳረዱ የተንኮል ሜራ
ጊዜውም ደረሰ የአባቱ ሰዓት
የናዝሬቱ እየሱስ የሚገለጥበት
ለድሆች ወንጌልን የሚሰብክበት
ፈውስ ተዓምራቱን የሚፈጽምበት
እነሆ ደረሰ ቃል ስጋ እንደሆነ የታወቀበት
ጠላት ተቃጠለ የሚያደርገው ጠፋው
በፈተና ሊጥል በተንኮል ቢያቅተው
አሁንም አሰበ የቀድሞ ሙያውን
መክሰስ ማሳረድን የነፍስ ግድያውን
ሴራውን ጀመረ መሲሁን ሊገድል
የሰውን ልጅ ተስፋ በእንጭጩ ሊያቃጥል
የአዳምን ዘር ሁሉ አበሳ ሊያበዛ
ከእግዚአብሔር ለይቶ ዘላለም ሊገዛ
ሃሳቡ የተሳካ ለሶስት ቀን መሰለ
መቃብሩን ዘጋ በድንጋይ ከለለ
መሲህ ሞቶ ቀርቶ መፍትሄ የሌለ
ለካስ ለዚህ ኖሯል ወየው ጉድ ተባለ
ሃሰት ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው ነውን?
ወይስ የተናገረው ቃል ወድቆ ያውቃልን?
በፍጹም እግዚአብሔር ታማኝ ነው ቃሉን የማይረሳ
ከክንዱ የወጣው የናዝሬቱ እየሱስ የይሁዳ አንበሳ
እንደተጻፈለት ሞትን ድል አድርጎ በህይወት ተነሳ
ከእንግዲህ ዲያብሎስ ስራው ተበላሸ
ሞትና ሲኦልም ኋይላቸው ሟሸሸ
የጽልመት ደመናም ከሰው ልጅ ላይ ሸሸ

ከቶማስ ፍቅሩ

# Sharing my Experience

The future depends on what we do in the present
Ghandi

Goals organize and direct you toward positive change. They provide a sense of purpose and enable accomplishments that build confidence. As you develop your health goals, make them smart:

- Walk 10 minutes three times a day.
- Eat more fruits, vegetables and whole grains.
- Relax everyday to rid your body of tension and stress.
- Maintain good health by taking time for prevention.
- Sleep 7 to 8 hours each night.
- Discover meaning and purpose in your life. (Spiritual well being)

Keep in mind that motivation does not come first. First you do something; then you become motivated to do more. To encourage motivation, create both long-term and short-term goals.

For example:
I will walk 30 minutes per days of the week to increase my energy level. (Long term Goal)
I will walk 10 minutes during my lunch break three days each week of this month. (Short term Goal)
This allows you to succeed in small steps and enjoy building on your achievements. Confidence in your ability to achieve your goals is an important predictor of success. Remember, change is a process. As you make changes, you will need time to practice new behaviors. A new behavior does not become second nature in a week or even a month. Slipping back into old habits is not uncommon when changing your life style to become healthier. Most people experience setbacks and discouragement from time to time. As you achieve your short-term goals, give yourself healthy rewards. Consider taking a relaxing nap, purchasing a new camera or book online at
www.ibexmarket.com or pampering yourself with a massage or manicure. To get started, record your long-term health goals for 2008 as I pointed above. As Mark Tawain pointed out "Old habits cannot be thrown out the upstairs window. They must be coaxed down the stairs one step at a time."

Take care of yourself
Until next time

Getachew Teklu

## The Ten Commandments of Human Relations.

1. Speak to people. There is nothing as nice as a cheerful word of greeting.

2. Smile at people. It takes seventy-two muscles to frown, only fourteen to smile.

3. Call people by name. Music to anyone's ears is the sound of his/her own name.

4. Be friendly and helpful.

5. Be cordial. Speak and act as if everything you do is genuinely a pleasure, and if it isn't, learn to make it so.

6. Be genuinely interested in people. You can like almost everybody if you try.

7. Be generous with praise. Cautious with criticism.

8. Be considerate with the feelings of others. There are usually three sides to a controversy: yours, the other fellow's, and the right one.

9. Be alert to serve. What counts most in life is what we do for others.

10. Add to this a good sense of humor, a dash of humility, and a big dose of patience, and you well be rewarded many times over through life.

Source: Be Your Best. Joyce Meyer Magazine (April 2007).

# የማርች 2008 ተጠማቂዎች እንኳን ደስ አላችሁ



ከህጻንነታቸው ጀምረው በዚች ቤተክርስቲያን በአንድነት አድገው ጌታን እንደግል አዳኝ አድርገው ተቀብለው ለውሃ ጥምቀት የበቁትን የቤተክርስቲያኗን ታዳጊ ወጣቶችንእና ወላጆችን እንዲሁም ይህችን ቤተክርስቲያንን እንኳን ደስ አላችሁ እንላለን



Photo by Getachew Irko

አዘጋጅ
ማርታ ታደሰ

ዲዛይን
ራሔል አርጋው

# የቤተክርስቲያኒቷ ፕሮግራም

መደበኛ የአምልኮ ጊዜ እሁድ ከ 10:30A.M - 1:00P.M
ወጣቶች ፕሮግራም ማክሰኞ ከ 7:00P.M - 9:00P.M
ሮብ ማታ የአምልኮ ጊዘ ከ 7:00P.M - 9:00P.M
ኀሙስ ማታ የፈውስ ፕሮግራምከ 6:00 P.M -9:00 P.M
የጸሎት ምሽት አርብ ማታ ከ 7:00P.M - 12:00P.M
ቅዳሜ ጠዋት የእህቶች ፕሮግራም ከ 10:AM –12:00P.M

## አድራሻችን


Ethiopian Evangelical Church
in Minnestoa
770 7th st. East
St.Paul, MN 55106
(651) 772 0216 or (651) 772 0234
www.eecmn.org